USAID
FROM THE AMERICAN PEOPLE

Ministry of Education

## በትምህርት ሚኒስቴርና በዩ.ኤስ.ኤ. ዓለም አቀፍ የልማት ተራድኦ ኤጀንሲ ትብብር በሪድ ሲኦ የተዘጋጀ

# በትምህርት ቤት ደረጃ የንባብ እና የጽሁፍ ክህሎት ማሻሻያ የተግባር መመሪያ



Save the Children

## The READ CO Project

Launched in January 2015, the USAID-funded Reading for Ethiopia's Achievement Developed Community Outreach (READ CO) is a four-year initiative to increase access to grade-level appropriate reading materials, provide children with opportunities to practice reading, and strengthen parental and community engagement in support of children's learning to read. This initiative supports the national READ Program effort to address the learning needs of 15 million primary grade students in seven (7) Ethiopian Languages (Amharic, Afaan Oromoo, Sidaamu Afoo, Af-Soomaali, Tigrinya, Wolayttatto and Hadiyyissa).

READ CO is implemented by Save the Children and its regional NGO partners Amhara Development Association (ADA), Tigray Development Association (TDA), Adult and Non-formal Education Association of Ethiopia (ANFEAE), the Organization for Welfare and Development in Action (OWDA) and the Save the Children South Hub (in SNNPR).

USAID
FROM THE AMERICAN PEOPLE

Ministry of Education

Reading for Ethiopia's Achievement Developed
Community Outreach (READ CO)
Cooperative Agreement No: AID 663-A-15-00003

### በትምህርት ሚኒስቴርና በዩ.ኤስ.ኤ. ዓለም አቀፍ የልማት ተራድኦ ኤጀንሲ ትብብር በሪድ ሲኦ የተዘጋጀ

# በትምህርት ቤት ደረጃ የንባብ እና የጽሁፍ ክህሎት ማሻሻያ የተግባር መመሪያ

**September 2016**

## DISCLAIMER

This Manual was produced with support from the U.S. Agency for International Development through USAID/Ethiopia READ CO, under Cooperative Agreement No. AID-663-A-15-00003.

This Publication was prepared by Save the Children. The author's views expressed in this publication do not necessarily reflect the views of the United States Agency for International Development or the United States Government.

Save the Children

## Acknowledgements

This manual was developed in consultation with experts nominated by the MOE, RSEBs, ZEDs and USAID/READ CO. Financial support for development of the manual was provided by USAID, and technical support and contributions were provided by the MOE and READ CO.

These experts developed the Working Manual for Master Trainers Training, Trainings of Level one and Level Two for /USAID/READ CO target schools and community. The manual is also used as a reference while implementing the school level and community level reading and writing activities. READ CO would like to thank all those who participated in this important effort. READ CO is grateful to each participant who shared their knowledge and skills', dedicating themselves to helping schools and communities to support children's reading, writing, speaking, and listening in their Mother Tongue languages.

### The Manual Development Working Group

Abera Mekonnen, SCI Education and Youth Head

Belainesh Woubshet, USAID /READ CO, Reading Materials Specialist

Belayneh Woldemariam | USAID/READ-Community Outreach Regional Program Manager

Carol DeShano da Silva (Dr.), Senior Advisor, Basic Education, Save the Children USA

Elias Ermias, USAID/READ CO Inclusion Specialist

Helen Boxwill, USAID/READ CO, International Reading Consultant

Mark Hamilton (Dr.), USAID/READ CO, COP

Mulugeta Deressa, USAID/READ CO, Community Outreach Specialist

Oumer Mohammed, SCI Education Program Specialist

Suadik Hassen, USAID/READ CO, COP

Tizazu Asare, SCI Education Head

### Reviewers

MOE SIP, and Mother Tongue and English Language Development Directorates, READ CO Local Languages Consultants, READ Core/Master Trainers

### READ CO and Partners

USAID/READ CO Team, TDA Team, ADA Team, ANFEAE Team, OWDA Team

### Designers

Asegid Senbu, Meskerem Eshetu, Netsanet K/Mariam

# ማውጫ


መግቢያ ........ 1

1. የንባብና የጽሁፍ ክበባት ........ 2

2. የንባብ ጥግ ........ 6

3. የትምህት ቤት የንባብና የጽሁፍ ክበብ በጎ ፈቃደኞች ........ 7

4. አጋዥ የንባብ መጽሀፍት ........ 10

5. በትምህርት ቤት ደረጃ ስሚከናወኑ ተግባራት ወላጆችና የማህበረሰቡ አባላት የሚያደርጉት ድጋፍ ........ 23

አባሪ ........ 24

# መግቢያ

ይህ በምህርት ቤት ደረጃ የንባብና የጽሁፍ የተግባር መመሪያ የተዘጋጀው ተማሪዎች የማንበብና የመጻፍ ክህሎቶችን እንዲማሩ ለማገዝ በሚደረገው እንቅስቃሴ ውስጥ የሚሳተፉ በጎ ፈቃደኞችና የአፍ መፍቻ ቋንቋ መምህራን የሚያደርጉትን ድጋፍና ተሳትፎ አቅጣጫ ለማስያዝ ታስቦ ነው፡፡ መመሪያው የንባብና የጽሁፍ ተግባራትን በትምህርት ቤት ውስጥ በዘላቂነት እንዴት መምራትና መደገፍ እንደሚቻል ያሳያል፡፡ በተጨማሪም የትምህርት ቤት ርዕሳነ መምህራን፣ ምክትል ርዕሳነ መምህራን፣ የጉድኝት ማዕከላት ሱፐርቫይዘሮችና የወላጅ፣ የመምህርና ተማሪ ህብረት በትምህርት ቤት ደረጃ የንባብና የጽሁፍ ክህሎት ማሻሻያ መርሀ ግብሮችን መደገፍ እንዲችሉ እገዛ ያደርጋል ተብሎ ታምኖበታል፡፡

መመሪያው አምስት ዋና ዋና ክፍሎችን አካቷል፡፡ እነርሱም፡-

1. የንባብና የጽሁፍ ክበባት
2. የንባብ ጥግ
3. በትምህርት ቤት ደረጃ የንባብና የጽሁፍ በጎ ፈቃደኞች
4. አጋዥ የንባብ መጻህፍት
5. በትምህርት ቤት ደረጃ የወላጅና የማህበረሰብ ድጋፍ

## 1. የንባብና የጽሁፍ ክበባት

የንባብና የጽሁፍ ክበባት ከመደበኛው ትምህርት በተጓዳኝነት የሚንቀሳቀሱ ሲሆን ከ1ኛ እስከ 4ኛ ክፍል የሚማሩ ህጻናት በንባብና በጽሁፍ ተግባራት የሚደራጁበት አሰራር ነው፡፡ የንባብና የጽሁፍ ክበብ በዋናነት ሦስት ንኡሳን ክፍሎችን ይዟል፡፡

ሀ. የንባብና የጽሁፍ ክበባት ዓላማ

ለ. የንባብና የጽሁፍ ክበባት ተሳታፊዎች

ሐ. የንባብና የጽሁፍ ክበባት አመራር

## 2. የንባብ ጥግ

የንባብ ጥግ ማለት በአፍ መፍቻ ቋንቋ የተዘጋጁ አጋዥ የንባብ መጻህፍት በመማሪያ ክፍል ውስጥ ጥግ ይዘው የሚቀመጡበት/የሚገኙበት ቦታ ነው፡፡ የንባብ ጥግ የሚከተሉትን መሰረታዊ ጉዳዮች በአጭሩ ያሳያል፡፡

- የንባብ ጥጉ ዓላማ- ለምን እንደሚደራጅ
- የንባብ ጥጉ አመራር እንዴት እንደሚካሄድ
- የንባብ ጥጉ ተጠቃሚዎች እነማን እንደሆኑና የንባብ ጥጉን ለምን ዓላማ እንደሚጠቀሙበት እንዲሁም የተሳታፊዎቹ ፍላጎትና ተነሳሽነት
- የንባብ ጥግ አጠቃቀም ክትትልና ድጋፍ

## 3. የትምህርት ቤት የንባብና የጽሁፍ ክበባት በጎ ፈቃደኞች

የትምህርት ቤት የንባብና የጽሁፍ ክበብ በጎ ፈቃደኞች የሚባሉት የአስረኛ ወይም የአስራ ሁለተኛ ክፍል ትምህርታቸውን ያጠናቀቁ፣ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት ህጻናት በሚማሩበት የአፍ መፍቻ ቋንቋ ማንበብና መጻፍ የሚችሉና የንባብና የጽሁፍ ተግባራትን ተከታታይነት ባለው መልኩ ለመምራትና ለማገዝ ፈቃደኞች የሆኑ ግለሰቦች ናቸው፡፡ እነዚህ በጎ ፈቃደኞች እድሜያቸው አስራ ስድስት ዓመት እና ከዚያ በላይ መሆን ያለባቸው ሲሆን ተሳትፎአቸውም የሴቶችን እና የወንዶችን ጥምርታ ያመጣጠነ መሆን ይኖርበታል፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ የአካል

ጉዳተኝነት ያለባቸው በጎ ፈቃደኞች ቅድሚያ ይሰጣቸዋል:: በዚህ ክፍል የበጎ ፈቃደኞች የስራ ድርሻ፣ የመመልመያ መስፈርትና የአመላመል ሂደት እንዲሁም የአመዳደብ ስልቶችና የማበረታቻ ስርዓት ተካተዋል::

## 4. አጋዥ መጻህፍት (በሀርድ ኮፒው ገጽ 2 የአማርኛው ቅጅ)

አጋዥ የንባብ መጻህፍት ማለት ከመደበኛ የመማሪያ-ማስተማሪያ መጻህፍት የተለዩና ንባብን ለመማርና ለማስተማር፣ለመለማመድና የንባብ ክህሎትን ለማሳደግ በአጋዥነት ጥቅም ላይ የሚውሉ መጻህፍት ናቸው:: አጋዥ የንባብ መጻህፍት ድምፀታዊ (ድምፆችን፣ ፊደላትንና ሆህያትን ከእይታ ቃላት ጋር )፣ ተነባቢ (የህጻናትን አዳምጦ የመረዳት ክህሎት ለማዳበር ለህጻናት የሚነበቡ) እና ደረጃ መጣኝ (ከአንደኛ እስከ አራተኛ የክፍል ደረጃን መሰረት ያደረጉ) በመባል በሦስት ይከፈላሉ:: በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የትምህርት ቤቶችና የማህበረሰቡ የአጋዥ መጻህፍት ፍላጎት፣ የአጋዥ መጻህፍት አቀማመጥና መገኛዎች፣ አጋዥ መጻህፍት ለንባብና ለጽሁፍ ክህሎት ልማት ያላቸው አስተዋጽኦ፣ ተማሪዎች፣ መምህራንና ማህበረሰቡ አጋዥ መጻህፍትን እንዴት መጠቀም እንደሚችሉ እና አጋዥ መጻህፍትን ከመደበኛው የመማር ማስተማር ሂደት ጋር አቀናጅቶ ለመጠቀም የሚረዱ ስልቶች ተካተዋል::

## 5. በትምህርት ቤት ደረጃ የወላጆችና የማህበረሰብ ተሳትፎ

የወላጆችና የማህበረሰብ ተሳትፎ ማለት በሥርዓተ-ትምህርቱ ውስጥ በተቀመጠው መሰረት ህጻናት የሚጠበቅባቸውን የእውቀት፣ የክህሎት፣ የአስተሳሰብና የባህሪ ፕሮፋይል ይዘው እንዲገኙ በመንከባከብም ሆነ በማሳደግ ረገድ ወላጆች ወይም የማህበረሰቡ አባላት በጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ የሚኖራቸውን ሚና የሚያሳይ የአሰራር ስርዓት ነው:: ህጻናት በትምህርት ቤት ውስጥ ማንበብን እንዲለማመዱና እንዲማሩ ህጻናቱን በማነጋገር፣ ለህጻናቱ በማንበብ፣ ጊዜ ሰጥቶ በማጫወትና ሌሎች ለንባብ ክህሎት ልማት አስፈላጊ ድጋፎችን በማቅረብ የህጻናትን የንባብ ክህሎት ለማሳደግ የወላጆችና የማህበረሰቡ ድጋፍ አስፈላጊ ነው::

በመሆኑም ወላጆችና የማህበረሰቡ አባላት በህጻናት የንባብ ክህሎት ልማት ላይ ትርጉም ያለው ተሳትፎ እና አስተዋጽኦ እንዲኖራቸውና ልጆቻቸውን በአግባቡ ያግዙአቸው ዘንድ ስለ ንባብ ክህሎት ምንነት፣ ጠቀሜታ እና የንባብ ክህሎት ልማት ሂደት መረጃ እና ግንዛቤ ማግኘት ይገባቸዋል:: ከዚህ አኳያ የአፍ መፍቻ ቋንቋ መምህራን፣ ርዕሳነ- መምህራን፣ ምክትል ርዕሳነ-መምህራን፣የጉድኝት ማዕከላት ሱፐርቫይዘሮች፣ የንባብና የጽሁፍ በጎ ፈቃደኞች ፣ተማሪዎች፣ወላጆችና የማህበረሰብ አካላት በትምህርት ቤት ደረጃ የንባብ ክህሎት ልማት ተግባራትን በአግባቡ መምራት እንዲችሉ ለማገዝ ነው ይህ መመሪያ የተዘጋጀው:: ወላጆችና የማህበረሰቡ አካላት ተሳትፎ የመጻህፍት መደርደሪያዎችን፣ የሚነበቡ መጻህፍትን፣ሽልማቶችንና ማበረታቻዎችን በገንዘብ ወይም በዓይነት በመለገስ ሊገለጽ ይችላል:: እንደዚሁም በትምህርት ቤት ደረጃ የንባብ ተግባራትን ለመደገፍ የገቢ ማሰባሰብና የተለያዩ ድጋፎችን በመስጠት መሳተፍ ይችላሉ::

# 1. የንባብና የጽሁፍ ክበባት

## 1.1. የንባብና የጽሁፍ ክበብ ምንነት

የንባብና የጽሁፍ ክበብ ማለት ከመደበኛው ትምህርት በተጓዳኝ ከ1ኛ እስከ 4ኛ ክፍል የሚማሩ ህጻናት በንባብና በጽሁፍ ተግባራት ለመሳተፍ የሚገናኙበት አደረጃጀት ነው:: ግንኙነቱም የትምህርት ቤት የንባብና የጽሁፍ ኮሚቴው ለክበቡ አባላት የንባብና የጽሁፍ ስራ ምቹ ሆኖ ባገኘውና በወሰነው ስፍራ በትምህርት ቤት ውስጥ የሚካሄድ ይሆናል:: የንባብና የጽሁፍ ተግባራትን ትምህርት በማይካሄድባቸው ትርፍ የመማሪያ ክፍሎች ወይም እንዳስፈላጊነቱ ከክፍል ውጭ ማካሄድ የሚቻል ሲሆን የንባብና የጽሁፍ ተግባራቱ የሚከናወኑባቸው ቦታዎች በተቻለ መጠን ለልጃገረዶችና የአካል ጉዳተኝነት ላለባቸው ህጻናት በቀላሉ ተደራሽ መሆን ይኖርባቸዋል::

## 1.2. የንባብና የጽሁፍ ክበባት

የማንበብና የመጻፍ ክበብ ዓላማ የማንበብና የመፃፍ ችግር ያለባቸውን ህፃናት በመለየት የማንበብና የመፃፍ ክሂል እንዲለማመዱና እንዲተገብሩ ለማድረግ ነዉ። ክበቡ ለእነዚህ ህፃናት ተጨማሪ ጊዚ በመስጠት፣ በፍላጎታቸው ላይ የተመሰረተ ተሰማሚ የማንበብና የመጻፍ ተግባራትን በማከናወን ከሚጠበቀው ደረጃ እንዲደርሱ ይረዳቸዋል።

የማንበብና የመጻፍ ክበብ ግብ የማንበብና የመጻፍ ችግር እንዳይከሰት ለማድረግና የማንበብና የመፃፍ ችግር ሲያጋጥም ማስተካከል ነዉ።

የክበቡ ዝርዝር ዓላማዎች፦

- የንባብና የጽሁፍ ችግር ያለባቸውን ተማሪዎች የመለየትና ድጋፍ የማድረግ።
- ለምሳሌ የመማር ችግር ያለባቸውን ተማሪዎች
- በመማር ወደኋላ የሚቀሩ ተማሪዎችን በተለይም ሴቶችና የአካል ጉዳተኞችን መለየትና መርዳት። ለምሳሌ የማንበብ ችግር ያለባቸውን ተማሪዎች በመለየት ማንበብና መፃፍ እንዲለማመዱ ማድረግ፤
- የተለየ የንባብ ክሂል ችግር ያለባቸውን ተማሪዎች በመለየት መደገፍ (ለምሳሌ የንግግር ድምጾች ግንዛቤ፤ የትዕምረተ ድምጾች ግንዛቤ፣አቀላጥፎ ማንበብ፣ የቃላት እውቀት). ለእዚህ ችግሮች ተጋላጭ ለሆኑ ተማሪዎች ትኩረት መስጠት።
- የተለየ የመጻፍ ክሂል ያላቸውን ተማሪዎች መደገፍ (ለምሳሌ፦ የፊደላትን አጣጣል፣ ክፍተት ጠብቆ መጻፍ፣ ስርዓተ ነጥብ በተገቢው ቦታ ያለመጻፍ፣ አመለካከትን/ራስን መግለጽ)
- የንባብና የጽሁፍ ባህል በትምህርትቤትና ከትምህርትቤት ውጭ እዲዳብር ማድረግ
- የንባብና የጽሁፍ ክህሎት መዳበር ከትምህርት ቤት የመማር ችሎታ ጋር እዲገናኝ ማድረግ
- የንባብና የጽሁፍ ክህሎት መዳበር የተለየ ጥቅም እንደሚያስገኝ መግለጽ (ለምሳሌ፦ እንደ መዝናኛ መረጃዎችን ለማግኘትና ከሌሎች ጋር ለመገናኘት)

## 1.3 የንባብና የጽሁፍ ክበብ ተሳታፊዎች

የንባብና የጽሁፍ ክበብ አባል ለመሆን ሁሉም ነፃ ነዉ። ይህ ማለት ጾታ፣ ዘር፤ ጎሳ፤ የአካል ጉዳት ያለበት በማለት ልዩነት አይፈጠርም። ሁሉንም ከ1ኛ እስከ4ኛ ክፍል የሚማሩ ህፃናት አባላት እንዲሆኑ ይጋበዛል። በክበቡ ውስጥ የሴቶችና የወንዶች ቁጥር የተመጣጠነ መሆን አለበት። (ከአባላቱ የሴቶቹ ድርሻ ቢያንስ ሃምሣ ፐርሰንት መሆን ይኖርበታል)። ማንኛውም ህፃን የማንበብና የመጻፍ ክበብ አባል መሆን ይችላል። ነገር ግን ክበቡ ትኩረት የሚያደርገዉ የማንበብና የመፃፍ ችግር ያለባቸውንና በደረጃው የሚጠበቀውን የንባብና የጽሁፍ ክህሎት ፕሮፋይል ማሟላት ያልቻሉትን ለመርዳት ነው።

በተለይ ከፍተኛ የማንበብና የመፃፍ ችግር ያለባቸው ህፃናት በዚህ ክበብ እንዲሳተፉ ይጋበዛሉ። የንባብና የጽሁፍ ክበብ አመራር ከፍተኛ የማንበብ ችግር ያለባቸውን ተማሪዎች ለመለየት ከመምህራን ጋር በመሆን የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም በትምህርት ቤት ደረጃ ተስማሚ የሆኑ ዝርዝር ደረጃዎች በማውጣት መለየት ይኖርባቸዋል።

የማንበብ ችግር ያለባቸዉን ህፃናት የመለየት ሂደት የሚከተሉትን ስልቶች ሊያካትት ይችላል፦

- አስቀድሞ ምንም የትምህርት ቤት ልምድ የሌላቸው የአንደኛ ክፍል ተማሪዎች ትኩረት መስጠት
- ትኩረት የሚደረግባቸው ተማሪዎች ከሚጠበቀው የንባብ ክሂል ያልደረሱ (ለምሳሌ፦ 1ኛ ክፍል ፊደል ለይቶ ማንበብ ያልቻሉ፤ 2ኛ ክፍል ማጠናቀቂያ በደቂቃ ከ35-55 ቃላት አቀላጥፎ ማንበብ ያልቻሉ)
- ትኩረት የሚደረግባቸው ተማሪዎች በሌሎች ምክንያቶች ከፍተኛ የማንበብ ችግር ያለባቸው (ለምሳሌ፦ በከፍተኛ ድህነት የሚኖሩ፣ የተመጣጠነ የምግብ እጥረት ያለባቸው)

## 1.4. የንባብና የጽሁፍ ክበብ አመራር

የትምህርት ቤት ም/ር/መምህር፣ የአፍ መፍቻ ቋንቋ መምህራን፤ በት/ት በቤት ደረጃ የማህበረሰብ በጎ ፈቃደኞች፣ ወመተህና የተማሪዎች ተወካይ በት/ት ቤት ደረጃ የንባብና የጽሁፍ ክበብን የሚመሩ አካላት ናቸው። የክበቡ ኮሚቴ ከ5-9 አባላት ይኖሩታል። የአመራር ኮሚቴው የጾታ ስብጥር የተመጣጠነ (50% ቢያንስ ሴቶች) መሆን አለባቸዉ። በተጨማሪም የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን ያካተተ መሆን አለበት። እንደ አስፈላጊነቱ ሴቶችና የአካል ጉዳተኞች የአመራር ሚናዉን ሊጫወቱ ይገባል።

የንባብና የጽሁፍ ክበብ አመራር ኮሚቴ የስራ ድርሻ/ ሃላፊነት፦

- በንባብና ጽሁፍ ክበብ የሚከናወኑ ተግባራትን በማቀድ መምራት
- መደበኛ የኮሚቴ ስብሰባ ማድረግ
- በክበቡ ስለሚከናወኑ ተግባራት ከት/ቤቱና ከማህበረሰቡ ጋር መነጋገር
- የንባብ ችግር ያለባቸውን ተማሪዎች ለመለየት ከክፍሉ የአፍ መፍቻ ቋንቋ መምህራን ጋር በመሆን መስፈርት ማዘጋጀት
- የንባብ ቡድን እንዲሁም የንባብ ጓደኞችን በመመልመል አንድ ላይ በመሆን መደበኛና ቋሚ የንባብ ፕሮግራም ማዘጋጀት
- የንባብና የጽሁፍ ውድድር ማዘጋጀት (የጥያቄና መልስ ጨዋታ) አሸናፊውን ማበረታታት
- የንባብና የጽሁፍ ክበብን በቀጥታ የሚያንቀሳቅሱ የአፍ መፍቻ ቋንቋ መምህራንና በት/ቤት ደረጃ መደገፍ
- ሴቶችና አካል ጉዳተኞች የማህበረሰብ የንባብ በጐ ፍቃደኞችን ያላቸውን ፍላጎት በመለየት ከት/ት ቤት አመራሩ ጋር በመሆን መደገፍ፤
- ሴቶችና የአካል ጉዳተኞችን ወጥነት ባለዉ መልኩ በመከታተልና በመደገፍ በክበቡ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ማድረግ፤
- በየሩብ አመቱ በትምህርት ቤት ደረጃ በንባብ ዙሪያ የተከናወኑ ተግባራትን መገምገም፤
- ኮሚቴው ቢያነስ በሳምንት አንድ ጊዜ እየተሰባሰበ በአመት 3 ጊዜ ከት/ት ቤት ማህበረሰብ ጋር እየተገናኘ ስለ ክበቡ ዕቅድ አፈፃፀም ዉይይት ያደርጋል።
- በመስከረም ወር በክበቡ አመታዊ ዕቅድ መወያየትና የማንበብ ችግር ያለባቸውን ተማሪዎች መለየት
- በየካቲት ወር ተሳትፎውን፣ አፈፃፀሙንና ዕድገቱን እንዴት እንደነበር መገምገምና የሚቀጥለውን መንፈቅ ዓመት ዕቅድ ማዘጋጀት፤
- በሰኔ ወር በአጠቃላይ በአመቱ የት/ት ዘመን የተከናወኑ ተግባራትን ሪፖርት ማድረግና አፈፃፀሙን መገምገም እንዲሁም ወደፊት ሊከናወኑ የሚገቡ ተግባራትን አትኩሮ ማሳየት፤

በንባብና ጽሁፍ ክበብ ስብሰባ ዝርዝር ይዘቱንና ተግባራቱን የሚወስኑት የንባብና የጽሁፍ በጎ ፈቃደኞችና የአፍ መፍቻ ቋንቋ መምህራን ናቸው። ቢያነስ ሁለት ፈቃደኛ የኮሚቴ አባላት የዕየለቱን የማንበብና የመጻፍ ክበብ የተግባር እንቅስቃሴ ማመቻቸት አለባቸው።

## 1.5. የንባብና የጽሁፍ ክበብ ተግባራት የክንውን ጊዜያት

የንባብና የጽሁፍ ክበብ አባላት በሳምንት ሁለት ቀን ለእያንዳንዱ የግንኙነት ጊዜ ለ90 ደቂቃ (በጠቅላለው በሳምንት ለሶስት ሰዓት) በበጎ ፈቃደኞችና የቋንቋ መምህራን አመቻችነት ይወያያሉ። የክበቡ የመወያያ ጊዜ የሚመረጠው የትምህርት ጊዜን ሳይነካ በአመቻቾቹ ነው።

## 1.6. በንባብና በጽሁፍ ክበብ የሚከናወኑ ተግባራት

የንባብና የጽሁፍ ክበብ ዋና ትኩረት የማንበብ ችግር ያለባቸውን ተማሪዎች በመለየት የንባብ ክህሎታቸውን እንዲያሻሽሉ መርዳት ነው፡፡ በመሆኑም ተግባራቱ የሚያተኩሩት ተማሪዎቹን እንደየችሎታቸው በመለየት ከአምስቱ ዋና ዋና የንባብ አላባውያን አንጻር (የንግግር ድምፆችን መለየትና መገንዘብ፣አቀላጥፎ ማንበብ፣ የቃላት እውቀት፣አንብቦ መረዳት) ወደ ተቀራረቢ ችሎታ እንዲደርሱ ማገዝ ነው፡፡ ከንባብና ጽሁፍ ክበብ ዓላማዎች አንዱ ህጻናት ትርጉም ባለው የንባብና የጽሁፍ ተግባር ተሰማርተው ብዙ ጊዜያቸውን እንዲያሳልፉ ማገዝና ማበረታታት በመሆኑ ሁሉም ክበቦች በግንኙነታቸው ወቅት ለንባብ (ድምጽ አሰምቶ ማንበብ፣ ተጋርቶ ማንበብ ወይም በጸጥታ/ ድምጽ ሳያሰሙ ማንበብ) እና ለጽሁፍ ስራ በቂ ጊዜ መመደብ ይኖርባቸዋል፡፡ ይህን ለማከናወን ለሚከተሉት ጉዳዮች ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል፡፡

ሀ. ተማሪዎችን ለንባብ ትምህርት ማደራጀት

ለ. የዘጠና ደቂቃውን ጊዜ አጠቃቀም በመከፋፈል ተማሪዎችን የተለዩና ዝርዝር የንባብ ክህሎቶችን ማስተማር

## ሀ. ተማሪዎችን ለንባብ ትምህርት ማደራጀት

ንባብን ለመማር የሚቸገሩ ወይም ለማንበብ የሚያዳግታቸው ህጻናት በሰለጠኑ መምህራን አማካይነት በነፍስ ወከፍ ደረጃ እገዛ ከተደረገላቸው ንባብን በቀላሉ ከመማር አንጻር በጣም ተጠቃሚዎች ይሆናሉ፡፡ ይሁን እንጅ በነፍስ ወከፍ ደረጃ ህጻናትን በሰለጠኑ መምህራን ንባብ የማስተማር አሰራርን መተግበር የማይቻልበት ሁኔታ ስለሚያጋጥም የንባብና የጽሁፍ ክበባትን የሚመሩ የአፍ መፍቻ ቋንቋ መምህራን ከንባብና ጽሁፍ በጎ ፈቃደኞች ጋር በመሆን ህጻናትን በንባብ ትምህርት ቡድኖች ማደራጀት ጠቃሚ አማራጭ ይሆናል፡፡ አደረጃጀቱ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን አማራጮች ያካትታል፡፡

- ተመሳሳይ ቡድን፦ በተመሳሳይ የንባብ ችሎታ ያሉ ተማሪዎች በንባብ ደረጃቸው በቡድን በማደራጀት ከዚያም መምህራን ወይም በጎፈቃደኞች የተማሪዎቹን ልዩ ፍላጎት መሰረት ያደረጉ ተግባራትን ማዘጋጀት፡፡
- ቅይጥ ቡድን፦ በተለያየ የንባብ ደረጃዎች የሚገኙ ተማሪዎችን በእኩል ቁጥር በማድረግ ቡድን መመስረት (ለምሳሌ በትምህርትቤት በአንድ ለአምስት አደረጃጀት መሰረት አንድ ከፍተኛ /ሞዴል አንባቢ፣ ሶስት ጀማሪ አንባቢ፣ አንድ መካከለኛ አንባቢ በማድረግ ማደራጀት ይቻላል)፡፡ በዚህ አደረጃጀት አማካይነት ዝቅተኛ ደረጃ አንባቢዎች ከከፍተኛ ደረጃ አንባቢዎች፣ ከፍተኛ ደረጃ አንባቢዎች ደግሞ ከሞዴል አንባቢዎች በመማር ክሂላቸውን ያዳብራሉ፡፡

## ለ. የ90 ደቂቃ ትምህርት አወቃቀር

በመጀመሪያ መምህራንና በጎፈቃደኞች አንድ ላይ በመሆን የማንበብና የመጻፍ ይዘቶችን በሰዓት ይከፋፍላሉ፡፡ በየክፍለጊዜው ለአንድ የንባብ እና የጽህፈት ክሂል መለማመጃ የማንበቢያ ጊዜ ይመደባሉ፡፡ ጊዜ ለመቆጠብ ሲባል መምህራንና በጎፈቃደኞች በዕለቱ የሚነበበውን ጽሁፍ በማንበብና በመጻፍ ክበብ ማዕክል ማስቀመጥ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህም ህጻናት የመጽሀፉን ሽፋንና ስዕሎችን በማየት የሚውቋቸውን ቃላት እንዲለዩ ለማድረግ ወይም መጽሀፉ እንደደረሳቸው ወዲያው እንዲያነቡ ለማረግ ይጠቅማል፡፡

ተማሪዎችን የተለየ የንባብ ክሂል ለማስተማር (ለምሳሌ፦ የፊደል እውቀት፣ ተነባቢዎችን መለየት፣አቀላጥፎ ማንበብ) መምህራን የክፍል ውስጥ ዘዴዎችን ወይም በሪድ ሲኦ ተጨማሪ የንባብ መጽሀፍ መመሪያ ወይም አጋዥ የማስተማሪያ ዘዴ መጠቀም ይችላሉ፡፡

ብዝሃነትን በተመለከተ እያንዳንዱ የክበብ ተግባር የሴቶችና የአካል ጉዳተኞችን ተሣትፎ ያረጋገጠ መሆን ይጠበቅበታል፡፡ ለአብነት ያህል የወንዶች የበላይነት ሊንጸባረቅ ወይም የአካል ጉዳተኝነት የሌለባቸው የአካል ጉዳተኛ በሆኑት ላይ የበላይነት ማሳየት አይፈቀድም፡፡

ሠንጠረዥ 1፡ የ90 ደቂቃ የንባብ እና የጽሁፍ ክበብ የአባላት ስብሰባና ዝርዝር ክሂሎችን የማስተማር ሁኔታ

| ለየቡድኖቹ የሚሰጡ ተግባራት | 90 ደቂቃዎች |
|---|---|
| የዕለቱን የንባብ መጽሀፍ መቃኘት | 10 ደቂቃዎች |
| የስብሰባውን አጀንዳ መወሰን | 5 ደቂቃዎች |
| በተማሪዎቹ ደረጃ መጽሀፉን ማንበብ/ቃላዊ ንባብ | 20 ደቂቃ |
| የተወሰነ የንባብ ክሂል ማስተማር (ምሳሌ፡ የፊደል አውቀት፣ ተነባቢ መጽሀፈ ማስነበብ) | 20 ደቂቃዎች |
| በህፃናት ደረጃ የተዘጋጀዉን መጽሐፍ ህፃናት ራሳቸዉን ችለዉ እንዲያነቡ ማድረግ | 15 ደቂቃዎች |
| ማቀናበርና መጻፍ (ለምሳሌ ቃላትን፣ አረፍተ ነገርን፣ አንቀጽን) ከመጽሐፉ ጋር ግንኙነት ያላቸዉ | 20 ደቂቃዎች |
| አጠቃላይ | 90 ደቂቃ |

*Source: Adapted from Reading Recovery Session Described in Slavin, et.al., 2009*

## 2. የንባብ ጥግ

### 2.1 የንባብ ጥግ ምንድን ነው?

የንባብ ጥግ በአፍ መፍቻ ቋንቋ የተዘጋጁ አጋዥ የንባብ መጻሕፍት/መሳሪያዎች የሚቀመጡበት የሚገኙበት ቦታ ማለት ነው። በንባብ ጥግ ለአጋዥ የንባብ መጻሐፍት መያዣ የሚያገለግል የመጽሀፍ መደርደሪያ መኖር አለበት። መጽሀፍ መደርደሪያ ከሌለ አጋዥ የንባብ መጻሕፍቱንና የመጻፊያ መሳሪያዎች ግድግዳ ላይ በሚንጠለጠሉ ሣጥኖች ወይም ኪሶች ሊያስቀምጧቸው ይችላሉ። በመደርዳሪያዎች ውስጥ የሚቀመጡት የአፍ መፍቻ ቋንቋ የንባብ መጻሕፍት/መሳሪያዎች በመምህራን፣ በተማሪዎች የተዘጋጁ ወይም ለማዘጋጀት ገቢያ የተገዙ ሊሆኑ ይችላል።

የንባብ ጥጉን ሌላ ተጨማሪ ሕንጻ መገንባት አያስፈልገውም። አጋዥ የንባብ መጻህፍቱን በመማሪያ ክፍሉ ውስጥ ለዚህ አገልግሎት በተዘጋጀ በአንድ ጥግ፣ ማስቀመጥ ይቻላል። ሆኖም የንባብ ጥጉ የተለያየ የአካል ጉዳተኝነት ላለባቸው ተማሪዎች በቀላሉ ተደራሽ መሆኑን ማረጋገጥ ይገባል።

### 2.2 የንባብ ጥጉ ዓላማዎች

- አጋዥ የንባብ መጻሕፍትን ለተማሪዎች ተስማሚ በሆነ ቦታ ለማስቀመጥ
- ከመማሪያ-ማስተማሪያ መጻሕፍት በተጨማሪ
- ተማሪዎች ማንበብና መጻፍ የሚያስችል ቦታ እንዲኖረቸው ለማድረግ፤
- የተማሪዎችን የማንበብና መጻፍ ክህሎት መሻሻል ስለሚያመቻችና በደስታ እንዲያነቡ ስለሚያበረታታ

### 2.3. የንባብ ጥግ አመራር

የንባብ ጥጉን ተማሪዎችና መምህራን በጋራ መምራት ይኖርባቸዋል። በአንድ ተመሣሣይ ክፍል ውስጥ የንባብ ጥግ የሚጠቀሙ መምህራንና ተማሪዎች የንባብ ጥጉን እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው መወያየትና መስማማት አለባቸው። በሁለቱም ፈረቃ የሚማሩ ተማሪዎች የንባብ ጥጉን የመቆጣጠር/የመምራት እኩል ሃላፊነት መውሰድ አለባቸው። በንባብ ጥጉ አመራር የሴቶቹና የወንዶች ቁጥር መመጣጠን አለበት። መምህራንም በንባብ ጥጉ አመራር መሳተፍ አለባቸው። በተመሳሳይ አካል ጉዳተኞች ካሉም ቅደሚያ ሊሰጣቸዉ ይገባል።

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ የንባብ ጥጐች አጠቃላይ እንቅስቃሴ በአፍ መፍቻ ቋንቋ መምህራን በተማሪዎች የጋራ ቅንጅት መመራት ይኖርባቸዋል። በተጨማሪም የንባብ ጥጉ የተማሪዎችን ማንበብና መጻፍ ክህሎትና ችሎታ ከማሻሻሉ ባሻገር ተማሪዎች መምራት/ማደራጀት እንዲለማመዱ ያደርጋል።

## 2.4. የንባብ ጥጉ ተጠቃሚዎችና ዓላማው

የንባብ ጥጉን የአፍ መፍቻ ቋንቋ መምህራን ለማስተማር ሲዘጋጁም ሆነ ሲያስተምሩ ሊጠቀሙበት ይችላሉ፡ የአፍ መፍቻ ቋንቋ መምህራን ንባብን በሚያስተምሩበት ጊዜ፣ ተረት ሲያስነብቡ፣ የተለያዩ የማንበብ ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎች በተለያየ የንባብ መመሪያ እንዲያነቡ ስያደርጉ ሊጠቀምቡት ይችላሉ። መምህሩ ግለሰባዊ የንባብ ችሎታን መሠረት ያደረገ የንባብ ትምህርት ለማስተማር የንባብ ጥጉን ሊጠቀም ይችላል።

ለምሳሌ መምህሩ አነስተኛ የአባላት ቁጥር ያለው (የንባብና የጽሁፍ ቡድን እያስተማረ ወይም እያገዘ ከሆነ የሌላውን ቡድን አባላት የንባብ ጥጉን እንዲጠቀሙ ማድረግ ይቻላል። በሳምንቱ መጨረሻም ለተማሪዎች መጽሀፍ ማዋስ ይችላሉ። የአፍ መፍቻ ቋንቋ መምህራን ሴቶችና የአካል ጉዳት ያለባቸውን ልጆች በተገቢው መማራቸውንና መጽሀፍ መዋሳቸውን ማረጋገጥ አለባቸው።

ተማሪዎቹ በንባብ ክፍለ ጊዜ ወይም ክፍል ስራ ሲሰጣቸው የንባብ ጥጉን መጠቀም ይችላሉ። ከዚህ በተጨማሪ በህዝብ በአላትና በሳምንቱ መጨረሻ ቀን ልጆች አጋዥ የንባብ መጽሀፍትን በመዋስ በትርፍ ጊዜያቸው ለራሳቸውና ለቤተሰቦቻቸው ማንበብ ይችላሉ።

## 2.5. የንባብ ጥጉ አጠቃቀም ክትትልና ድጋፍ

መምህራን እና ተማሪዎች የመጽሀፍ ማዋሻ መከታታያ ቅጽ በማዘጋጀት ተማሪዎች አጋዥ የንባብ መጽሀፉን እንዴት እንደሚዋሱ፣ እና እንደሚጠቀሙ፣ መቼ እንደሚመልሱና እንዴት መጽሀፉን እንደሚይዙ፣ የትኛው መጽሀፍ ይበልጥ ተወዳጅ እንደሆነ፣ መጽሀፉን እቤታቸው ማንበብ አለማንበባቸውን ክትትል ያደርጋሉ (የመጽሀፍ ማዋሻ ቅጹን ከአባሪው ይመልከቱ)። የትምህርትቤቱ ርዕሰ መምህር ወይንም ም/ር/መምህር በንባብ ጥጉ የሚገኙ የንባብ መሳሪያዎች ያሉበትን ሁኔታ በመከታተል በመደገፍ ከንባብና የጽሁፍ ክበብ ተግባራት ጋር ቅንጅት እንዲኖር ያደርጋሉ። ከዚህ አንጻር የአፍ መፍቻ ቋንቋ መምህራንና የንባብና የጽሁፍ ክበብ በጎ ፍቃደኞች የተደራጀ የአእምሮ ማነቃቂያ ጥያቄዎች እና ሳምንታዊ የውይይት መድረኮች በማዘጋጀት የማንበቢያ ጥጉን ተጨማሪ ንባብ አካሄድ ግልጽ የማድረግ ሃላፊነት አለባቸው። በተጨማሪም የትምህርትቤትና የክላስተር ሱፐርቫይዘሮችም የንባብ ጥጉ ያለበትን ሁኔታ፣ ያሉትን አጋዥ ንባብ መጽሀፍ አይነቶች፣ የንባብና የጽሁፍ ክበብ ተግባራትንና የመጽሀፍ ማዋሻ ክትትሉን ማየትና ማረጋገጥ ይጠበቅባቸዋል። ለዚህ ሥራቸው ውጤታማነትም በትምህርት ቤት ሱፐርቪዥን (የድጋፍ አገልግሎት) የክትትልና ግምገማ ቼክ ሊስት ውስጥ የንባብ ጥግ አጠቃቀም ጉዳየን ማካተት ይጠበቅባቸዋል። በተጨማሪም የአፍ መፍቻ ቋንቋ መምህራንና የንባብና የጽሁፍ ክበብ በጎፈቃደኞች ሴቶችና የአካል ጉዳተኞች በማንበቢያ ጥጉ በተገቢው መንገድ እየተጠቀሙና እየተሳተፉ መሆኑን ክትትል ማድረግና ማበረታታት ይጠበቅባቸዋል። ለምሳሌ፦ የንባብ ጥጉን ለመጠቀምና መጻህፍቱን ለማዋስ ችግሮች ቢፈጠሩ ከትምህርትቤት ርዕሰ መምህራን ጋር በመሆን ችግሩን ለመፍታት ሃላፊነት ይወስዳሉ።

# 3. የትምህት ቤት የንባብና የጽሁፍ ክበብ በጎ ፈቃደኞች

የትምህትቤት የንባብና የጽሁፍ ክበብ በጎፈቃደኞች 10ኛና 12ኛ ክፍል ያጠናቀቁና ማንበብና መጻፍ የሚችሉ፣ በት/ቤታቸው የንባብ ተግባራቱን ቀጣይነት ባለው መልኩ መምራትና መደገፍ የሚችሉ፣ አካላት ናቸው። እነዚህ በጎ ፈቃደኞች የትምህርት ቤቱን የንባብና የጽሁፍ ክበብ በማመቻቸት ይደግፋሉ። ነገር ግን ከክልል ክልል ወይም ከማህበረሰብ ማህበረሰብ ሊለያዩ ይችላሉ። የበጎ ፈቃደኞቹ ዕድሜ 16 ዓመትና በላይ እንዲሆን ይጠበቃል። ከበጎ ፈቃደኞቹ ሴቶቹ ቢያንስ 50% ፐርሰንት እንዲሆኑ ይጠበቃ። በተጨማሪም አካል ጉዳተኞች ካሉ በጎ ፈቃደኞች ቢሆኑ ሌሎችን አካል ጉዳተኞች ይደግፋሉ።

## 3.1. የትምህርት ቤት የንባብና የጽሁፍ ክበብ በጎ ፈቃደኞች የመምረጫ መስፈርቶች

የሚከተሉትን የመምረጫ መስፈርቶች የሚያሟሉ በጎ ፈቃደኛ መሆን ይችላል፡፡

- ለበጎ ፈቃደኞች የሚሰጠዉን ስልጠና የወሰደ/ች
- ለንባብና ጽሁፍ ክበብ በጎ ፈቃደኛ ለመሆን ፈቃደኛ የሆነ/ች
- ዕድሜው/ዋ ከ16 ዓመትና በላይ የሆነ/ች በሚያገለግለው/በምታገለግለው ማህበረሰብ የሚኖር/የምትኖር
- ከተቻለ አንድ ወንድና አንዲት ሴትካልሆነ ደግሞ ሁለት ወንዶች ወይም ሁለቱም ሴቶች አካል ጉዳትኛ ሊሆኑ ይችላሉ
- ከተቻለ በጎፈቃደኞቹ ሴቶች ሊሆኑ ይችላሉ
- በአፍ መፍቻ ቋንቋ መናገር እና መረዳት፣ አዳምጦ መረዳት፣ መጻፍ እና አቀላጥፈው ማንበብ የሚችሉ፣ ማንኛውንም በቋንቋው የሚተላለፈውን መመሪያ በሚገባ መረዳት የሚችሉ መሆን ይገባቸዋል፡፡
- የንባብና የጽሁፍ በጎ ፍቃደኞች የንባብና የጽሁፍ ክበቡን በቋሚነት ለመደገፍ ቁርጠኞች መሆን ይጠበቅባቸዋል (ለምሳሌ፦ በሣምንት ሁለት ቀን)

## 3.2. የትምህርት ቤት የንባብና የጽሁፍ ክበብ በጎ ፈቃደኞች የምልመላ ሂደት

- መስፈርቱን የሚያሟሉ፣ ወይም በበጎ ፍቃደኝነት ማገልገል የሚፈልግ፣ የሆነ እና ሆኖ ለመስራት ዝግጁ የሆነ ማንኛውም ሰው በስብሰባው ተገኝቶ ንባብና ጽሁፍ ክበብ መተዋወቅና ውይይት ማድረግ እንደሚችል መጠየቅ
- የስብሰባው አመቻቾች ከቀትስቦ/ወመተህ የተወጣጡ አፍ መፍቻ ቋንቋ መምህራን ወይም በትምህርትቤት ርዕሰ መምህር የሚደገፉ ይሆናል፡፡ የማህበረሰቡ መሪ የንባብና የጽሁፍ ክበብ አባላትን ከላይ በተጠቀሰው መሰረት ይለያሉ፡፡ ማንበብና መጻፍ የሚችሉና በበጎ ፍቃደኝነት መሣተፍ የሚችሉ ማንኛውም የማህበረሰቡ አባላት ለዚህ ሥራ ይጋበዛሉ፡፡
- በተለያየ አጋጣሚ በጎፈቃደኛ የሆኑ/የነበሩ የንባብና ጽሁፍ ክበብ አባላት ቅድሚያ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡
- በሴቶችና በአካል ጉዳተኞች የንባብና ጽሁፍ መፃፍ ክበብ በጎ ፈቃደኞች ቅድሚያ ሊሰጥ ይገባል፡፡

## 3.3. ለትምህርት ቤት ተኮር የንባብና ጽሁፍ በጎ ፈቃደኞች መመልመያ ስልቶች

የመመልመያ ስልቶቹ ከትምህርት ቤት ትምህርት ቤት ይለያያሉ፡፡ የመመልመያ ስልቶች የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፦

- አስቀድሞ የነበሩ ቡድኖች፦ በአንዳንድ ትምህርት ቤቶች ከዚህ ቀደም በበጎ ፍቃደኝነት የሰሩ የነበሩ ቡድኖች ሊኖሩ ስለሚችሉ፤ የትምህርት ቤት ርዕሰ መምህራን፣ ቀትስቦ/ወመተህ ቀድመው የነበሩትን ቡድኖች የመለየት ስራ ማካሄድ ይኖርባቸዋል፡፡
- ራስን መምረጥ/ግለ ምርጫ፦ ትምህርት ቤቱ ስብሰባ በመጥራት በበጎፈቃደኝነት የማገልገል ፍላጐት ተግባርና ኃላፊነት በማስረዳት ተማሪዎች በፍቃዳቸው አባል እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡
- በህዝብ ምርጫ፦ ህብረተሰቡን ስብሰባ በመጥራትና ጥቆማ እነዲደረግ በማድረግ ብዙ ድጋፍ ያላቸውን ማስመረጥ
- በትምህርትቤቱ መሪዎች፦ በቅድሚያ የተወሰኑ በጐፈቃደኞችን በመምረጥ እነዚህ በጐ ፍቃደኞች በተወሰኑ ቦታዎች ብቻ ተዘዋውረው በመቀሳቀስ ሌሎች በጐፈቃደኞችን እንዲመጡ መደገፍ
- በትምህርት ቤቱ /በማህበረሰቡ መሪዎች መሰየም፦የትምህርት ቤቱ/የማህበረሰቡ መሪዎች እንደጠቁሙ በማድረግ፤

## 3.4. የንባብና የጽሁፍ ክበብ በጎ ፈቃደኞች የስራ ድርሻና ሃላፊነት

- ለንባብና ጽሁፍ ክበብ በጎ ፈቃደኞች እና ተሳታፊዎቹ ምቹ ቦታና ጊዜ ማመቻቸት
- ለንባብና ጽሁፍ ክበብ ተግባራትና ሂደቶች ዕቅድ ማዘጋጀት
- ለንባብና ጽሁፍ ክበብ ተሣታፊ ህጻናትን በአዎንታዊ መልክ መደገፍና መከታታል
- በክበቡ የሚሳተፉትን ተማሪዎችን መረጃ መዝግቦ መያዝ
- የንባብና ጽሁፍ ክበብ እንቅስቃሴ፣ ያጋጠሙ ችግሮች የተገኙ ውጤቶች ወርሃዊ ሪፖርት ማድረግ
- የማንበብ የመጻፍ ችግር ያለባቸውን ተማሪዎች ችግር ከሌለባቸው ተማሪዎች መለየትና ችግር ያለባቸውን መደገፍ
- ከአፍ መፍቻ ቋንቋ መምህራን፣ ወመተህ ከንባብና ጽሁፍ ክበብ ጋር በመሆን ሴቶችንና አካል ጉዳተኞችን በክበቡ ንቁ ተሳትፎ እንደያደርጉና የንባብ ቁሳቁስ እንደያገኙ መደገፍ፤
- ሴቶችና አካል ጉዳተኞች በንባብና ጽሁፍ ክበብ ያላቸውን ተሳትፎ በማጉላት በማህበረሰቡ ግንዛቤ መፍጠር

## 3.5. ለት/ቤት ተኮር የንባብና ጽሁፍ ክበብ በጐ ፍቃደኞች የሚሰጥ ማበረታቻ

ለንባብና ጽሁፍ ክበብ በጎ ፈቃደኞችከሚደረጉ የተለያዩ ማበረታቻዎች ውስጥ የሚከተሉት ጥቂቶቹ ናቸው

- በሪድ ሲ ኦ ወይም በመንግስታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ አጋሮች አማካይነት ያልሆነ ትምህርት ላይ የሚዘጋጁ ደስልጠናዎች ማግኘት
- በአፈጻጸም የተሻለ የሰሩ የንባብና የጽሁፍ ክበብ በጎ ፈቃደኞች የቀጣይ የትምህርት ዕድል
- ለንባብና ጽሁፍ ክበብ በጎ ፈቃደኞች ለሰሩት ስራ የእውቅና የምስክር ወረቀት ይሰጣል
- ከትምህርት ቤት/ ከመንግስት ገንዘብ የሚገኝ ከሆነ ለበጎ ፈቃደኞቹ የገንዘብ ወይንም ገንዘብ ነክ ያልሆነ ድጋፍ እንደ መጓጓዣ፣ የምሳ ግብዣ የመሳሰሉትን ውጭዎች ይሸፍናል።
- የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር፣ቀትስቦ /ወመተህ በጎፈቃኛቹ ስልጣና ከመውሰዳቸው በፊት ጥቅማጥቅሞችን በተመለከተ በቅድሚያ ውል ይገባል።

## በጎ ፈቃደኞቹ ከተመለመሉ በኋላ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናሉ።

- ከንባብና ጽሁፍ ክበብ ኮሚቴዎች ጋር በመሆን ከ1-4ኛ ክፍል የሚማሩ ተማሪዎች በንባብና ጽሁፍ እንዲሳተፉ ይጋበዛሉ።
- ለማንበብ ፍላጎት ያላቸውንና የማንብብና መጻፍ ችግር ያለባቸውን ተማሪዎች ይለያሉ፤
- በጎፈቃደኞቹ ተማሪዎቹን እንደፍላጎታቸው ይመድባሉ፤
- ለተማሪዎቹ ንባብና ጽሁፍ ክበብ መረጃ በመስጠትከወላጆቻቸው መረጃ እንዲሰበስቡ ያደርጋሉ
- የማንበብና የመጻፍ ተግባራቱን ከልጆቹ ጋር ይጀምራሉ።
- ልጆቹ የተለያየ የንባብ ተግባራትን እንደያከናውኑ ያደርጋሉ።
- የልጆቹን የንባብ ለውጥ ይመዘግባሉ
- በየሁለት ሳምንቱ ስለ ልጆቹ ለት/ት ቤቱ ሪፖርት በማድረግ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን ይደግፋሉ።
- ጥሩ አንባቢዎች ደካማ አንባቢዎችን እንዲደግፉ ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ
- አጋዥ የንባብ መጻሕፍት በንባብና መጻፍ ክበባቱ ከተነበቡ በኂላ ወደ ንባብ ጥጉ መመለሳቸውን ያረጋግጣሉ፤
- ከአፍመፍቻ ቋንቋ መምህርና ከትምህርት ቤቱ ጋር በመተባበር ጥሩ አንባቢዎችን በየሩብ አመቱ ይሸልማሉ፤

በመጨረሻም በየሩብ አመቱ የንባብና ጽሁፍ ክበቡ አተገባበር፣ አመራርና ክትትል እንዴት እንደነበረ ይገመግማሉ።

# 4. አጋዥ የንባብ መጽሀፍት

ይህ ክፍል ለአፍ መፍቻ ቋንቋ መምህራን፣ ለርዕሳነ መምህራን፣ ለምክትል ርዕሳነ መምህራን፣ ለትምህርት ቤትና የጉድኝት ማዕከላት ሱፐርቫይዘሮች፣ ለተማሪዎችና ስልጠና ለወሰዱ በጎ ፈቃደኞች አጋዥ የንባብ መጻህፍትን በመጠቀም ተማሪዎች ማንበብ እንዲማሩ እንዴት ማገዝ እንደሚቻል መረጃ በመስጠት ግንዛቤ ያስጨብጣል። መረጃዎቹም፦

1. ስለ አጋዥ የንባብ መጻህፍትና በንባብ ክህሎት እድገት ላይ ስለሚኖራቸው ድርሻ፣
2. በሪድ ሲኦ ፕሮጀክት እና በትምህርት ሚኒስቴር የጋራ ትብብር ስለተዘጋጁ አጋዥ መጻህፍት ዓይነት እና
3. ንባብን በማህበረሰብ ደረጃ ለማስተዋወቅ የሚረዱ ዝርዝር ስልቶች።

## 4.1. የአጋዥ ንባብ መጻህፍት ምንነት

በትምህርት ሚኒስቴር የአጋዥ መጻህፍት ዝግጅትና መምረጫ መመሪያ መሰረት አጋዥ መጻህፍት የሚባሉት መደበኛ የመማሪያ-ማስተማሪያ መጻህፍት ያልሆኑና ንባብን ለመማር፣ለማስተማር፣ ለመለማመድና የንባብ ክህሎትን ለማሳደግ በአጋዥነት ጥቅም ላይ የሚውሉ ግብዓቶች ናቸው። አጋዥ የንባብ መጻህፍት በዓይነት ሦስት ሲሆኑ እነርሱም ድምፀታዊ (ድምፆችን፣ ፊደላትንና ሆህያትን ከእይታ ወይም ከተዘውታሪ ቃላት ጋር )፣ ደረጃ መጣኝ (ከአንደኛ እስከ አራተኛ የክፍል ደረጃን መሰረት ያደረጉ) እና ተነባቢ (የህጻናትን አዳምጦ የመረዳት ክህሎት ለማዳበር ለህጻናት ድምጽ አሰምቶ ወይም ጮክ ብሎ ማንበብ) በመባል ይመደባሉ። የድምጸታዊና የደረጃ መጣኝ አጋዥ መጻህፍት ተተራኪ ወይም መረጃ ሰጭ ይዘቶች አሏቸው። እነዚህ መጻህፍት ከአንደኛ እስከ አራተኛ ክፍል ለሚማሩ ህጻናት የሚያገለግሉ ናቸው። መጻህፍቱም በሪድ ሲ ኦ ፕሮጀክት የሚደገፉ ሰባቱን የአፍ መፍቻ ቋንቋዎች (ሀድይኛ፣ ወላይትኛ፣ ሲዳምኛ፣ አማርኛ፣ ኦሮምኛ፣ ሶማሊኛ እና ትግርኛ) የሚናገሩ ህጻናት ማህበራዊና ባህላዊ ሁኔታዎችን በጠበቀ መልኩ የተዘጋጁ ናቸው።

## 4.2. ሪድ ሲኦ ያዘጋጃቸዉ የአጋዥ የንባብ መጽሀፍ ምንነት

ሀ. ድምፀታዊ አጋዥ የንባብ መጻሕፍት፤ ከሥርዓተትምህርቱ ጋር ቀጥተኛ ግንኙት ያላቸው ሆነው ተማሪዎች የተማሯቸውን ፊደሎችና ተዘውታሪ ቃላት ብቻ የያዙ ናቸው። ድምፀታዊ አጋዥ መጻሕፍት የድምጾችንና ፊደላትን ግንኙነት የሚያሳዩ የተለመዱ ቃላትን ይይዛሉ። (ይህም ማለት አንድ ፊደል አንድ ድምጽ)

ለ. ደረጃ መጣኝ አጋዥ የንባብ መጻሕፍት፤ ማንበብን የሚማሩና የሚለማመዱ ተማሪዎችን ለማገዝ በዓይነት የተለያየ የክብደት ደረጃዎች ያሏቸውን ታሪኮች የያዙ ናቸው። በእነዚህም የሚካተቱት የቃላት ብዛት፣ የዓረፍተነገር መዋቅር፣ ይዘት፣ ስዕሎች፣ የፊደላት መጠንና የመልክ ዓይነትና ሌሎች ጉዳዮች የንባቡን ደረጃና የመጽሐፉን ተገቢነት ወይም ትክክለኛነት ይወስናሉ። ትምህርት ሚኒስተር ለአንደኛ እስከ አራተኛ ክፍል አጋዥ የንባብ መጽሕፍት ለእያንዳንዱ ክፍል ባለሁለት ደረጃ መጣኝ ስርዓት (ደረጃ ሀ እና ደረጃ ለ) አዘጋጅቷል።

ሐ. ተነባቢ አጋዥ የንባብ መጻሕፍት፤ ሪድ ሲኦ በትምህርትቤት፣ በቤትና በማህበረስብ ደረጃ ለልጆች የሚሆኑ ተነባቢ ንባብ መጻሕፍት አዘጋጅቷል። በተጨማሪም ሁለቱንም ድምፀታዊ እና ደረጃ መጣኝ አጋዥ መጽሀፍትን ለተማሪዎች በተነባቢ ንባብ ማንበብ ይቻላል። የተነባቢ አጋዥ የንባብ መጻሕፍት ዋና ዓላማ ራሳቸዉን ችለዉ ማንበብ ለማይችሉ ህፃናት መጽሐፉ ሲነበብ እንዲሰሙ ለመጋበዝ ነዉ። ተነባቢ መጽሀፍ ቀድሚያ የሚጠቅመው ለተነባቢ የንባብ ተግባራት ነው።

## 4.3. ማህበረሰቡ ምን ያህል አጋዥ የንባብ መጽሐፍ ይፈልጋል?

ለህፃናት በተለያዩ የክብደት ደረጃዎች የተዘጋጁ ተስማሚና የተለያዩ የጽሑፍ ዘውጎች (ልብውለድ፣ ኢልብወለድ) ተደራሽ ማድረግ ይገባል። በሪድ ሲኦ ፕሮጀክት የእያንዳንዱ ትምህርትቤት የማንበቢያ ጥግ 100 ርዕሶችን፣ የማህበረሰብ መጻሕፍት ባንኮች 100 ርዕሶችን በአካባቢው የአፍመፍቻ እና በማስተማሪያ ቋንቋ የተዘጋጁ መጽሀፍትን ይይዛሉ።

## 4.4. የአጋዥ የንባብ መጻሕፍት ማስቀመጫ

አጋዥ የንባብ መጻሕፍት የሚቀመጡት በአፍመፍቻ ቋንቋ መማሪያ ክፍል ውስጥ በሚገኝ የንባብ ጥግ ነው:: የንባብ ጥጉች የክፍል ውስጥ ቤተመጽሀፍት በመባል ይታወቃሉ::

## 4.5. አጋዥ መጻህፍት ለንባብና ለጽሁፍ ክህሎት እድገት ያላቸው ጠቀሜታ

አጋዥ መጻህፍትን በብዛት ለተማሪዎች ተደራሽ ማድረግ በህጻናቱ የንባብና የጽሁፍ ክህሎት መሻሻል ላይ የሚኖረው ድርሻ የላቀ ሲሆን ይህም በብዙ መልኩ ይገለጻል:: የአጋዥ የንባብ መጻህፍት በትምህርት ቤት ውስጥ መገኘት ትምህርት ቤቱን በሚነበቡ መጣጥፎች የበለጸገ የትምህርት አካባቢ እንዲሆን ያደርገዋል:: ይህም ህጻናት ስለ ሚነበቡ ጽሁፎች የሚኖራቸውን ጽንሰ ሀሳብ ያሳድጋል:: ህጻናት መጻህፍትን በማየትና በመነካካት ስለ መጻህፍቱ አወቃቀር (ለምሳሌ ስለ መጽሐፉ የሽፋን ገጽ እና ርዕስ) እንዲሁም ስለ መጻህፍቱ ዓላማ መረዳት ይችላሉ:: በሌላ በኩል አጋዥ መጻህፍትን ተደራሽ በማድረግ የተማሩ ጎልማሶች ወይም ላቅ ያለ የማንበብ ችሎታ ያላቸው ተማሪዎች ለህጻናት ታስበው የተዘጋጁና የሚነበቡ ተረቶችን እንዲያነቡላቸው ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል::

ድምፅ አሰምቶ (ጮኽ ብሎ) ማንበብ የንግግር ቋንቋን ለማሻሻል (የቋንቋ ድምፆችን፣ ቃላትንና አባባሎችን ለመለየት) ይጠቅማል:: ይህም ንባብን ለመማር እና አቀላጥፎ የማንበብ ክህሎትን በማሳደግ ረገድ ወሳኝ ሚና ይጫወታል:: ትክክለኛውን የአነባበብ ደንብና ሥርዓት (አገላለጽና የድምጽ አወጣጥ፣ ፍጥነትና ቅልጥፍና) መሰረት አድርጎ ሚያነብ አንባቢን አዘውትረው የሚያዳምጡ ህጻናት ታሪኩ በተነበበት ሁኔታ፣ ትክክለኛ ወይም ተመሳሳይ ቅላጼ፣ፍጥነትና ቅልጥፍናን ተከትለው ማንበብን የመማር እድላቸው ይሰፋል:: አጋዥ የንባብ መጻህፍትን ለህጻናት ተደራሽ በማድረግ ህጻናት ለማንበብ ያላቸውን ፍላጎት በማነሳሳት ንባብን እንዲለማመዱና እንዲወዱ ለማድረግ ያግዛል::

በመሆኑም መደበኛውን የንባብ ትምህርት ለማገዝና የተለያየ የማንበብ ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎች እንደየችሎታቸው ለመርዳት ሲባል መምህራን አጋዥ መጻህፍትን በመማሪያ ክፍል ውስጥ መጠቀም ይችላሉ::

**አጋዥ የንባብ መጻሕፍትን መደበኛ ካልሆነው አቀራረብ ጋር የማቀናጀት ስልት**

ውጤታማ የንባብ ትምህርት ተማሪ ተኮርና ማራኪ መሆን ይገባዋል:: በሌላ አባባል ተማሪዎች በትምህርቱ ሂደት ትርጉም ያለው ተግባር ማከናወንና በንቃት መሳተፍ ይኖርባቸዋል::

ይህ የሚከናወነው መመሪያን መሰረት በማድረግና በብልሃት ነው:: የአጋዥ ንባብ መጽሀፉን ይዘት የበለጠ መረዳት የሚቻለው የቅድመንባብ፣የንባብ ጊዜና ድህረ ንባብ ብልሃትን መጠቀም ሲቻል ነው:: ይህ ክፍል መምህራንና የትምህርት ቤት በጎፈቃደኞች ተማሪዎችን ለማንበብ ሲያስተምሩ ሊጠቀሙበት የሚችሉትን አንዳንድ ብልሀቶችን ያብራራል:: በአባሪው ውስጥ የመረዳት ዝርዝር ብልሀቶች፣ ተማሪዎቹ የሚያሻሽሉት የንባብ ክሂል፣መምህራን ወይም በጎፈቃደኞች የሚጠቀሙበት አጋዥ የንባብ መጽሀፍ፣ ብልሃቱን የሚተገብሩ ተስማሚ የክፍል ደረጃዎች ይገኛሉ::

## ከንባብ በፊት፣ በንባብ ጊዜና ከንባብ በኋላ የሚቀርቡ የንባብ ጥያቄዎች

ከንባብ በፊት ፣ በንባብጊዜ፣ ከንባብ በኂላ የንባብ ጥያቄዎች መጠየቅ የተማሪዎቹን ቀደመ እውቀት በመቀስቀስ የተማሪዎችን አንብቦ መረዳት በማፋጠን በኩል እገዛ ያደርጋል:: ጥያቄዎቹ ለሁሉም የክፍሉ ተማሪዎች፣ በቡድን፣ ወይም ለጥንድ ሊዘጋጅ ይችላል:: የበለጠ ጥቅም የሚኖረው ተማሪዎች በንባብ ጊዜ ጥያቄዎችን ራሳቸውን እጠየቁ ሲያነቡ ነው::

| | ዓላማ | ምሳሌያዊ ጥያቄዎች |
|---|---|---|
| የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች | የቀደመ እውቀት መቀስቀስ | የመጽሀፉ ርዕስ የምወደው እንስሳ ነው፡፡<br>የሚወደውን/የምትወደውን እንስሳ የሚነግረኝ/የምትነግረኝ ማነው/ማናት? |
| | ስለምንባቡ መገመት | የመጽሀፉ የሽፋን ስዕል ምንድን ነው? ስዕሉን ከተመለከታችሁ በኋላ፣ መጽሀፉ ስለምን የሚያወራ ይመስላችኋል? |
| | ከአዳዲስ ቃላት ጋር መተዋወቅ | ይህ መጽሀፍ "ጠንቃቃው" ድመት ተብሎ ይጠራል፡፡ "ጠንቃቃ" የሚለውን ቃል ትርጉም የሚነግረኝ አለ? ጉጉ ለሚለው ሌላ ተመሳሳይ ቃል የሚነግረኝ አለ? |
| የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች | ለመገመት(መተንበይ) | ቀጣዩ ምን የሚሆን ይመስላችኋል? እንዴት? |
| | ታሪኩን ከራስ ጋር መስተሳሰር(ማያያዝ) | ገጸባህሪውን ብትሆኑ ምን ታደርጉ ነበር? |
| | ከተባለው ያልተባለውን ለማግኘት መመራመር | ገጸ ባህሪው ምን የተሰማውይመስላችኋል?<br>እንዴት አዎቃችሁ? |
| | መረዳትን ለመከታተል | ከዚያስ ምን ይፈጠራል? (ቤቱን ሄደ፡፡ ) (ሌላ ተመሳሳይ ጥያቄ መተካት ይቻላል፡፡ |
| የድህረ ንባብ ጥያቄዎች | ዋና ሃሳቡን ለማግኘት | የታሪኩ ዋና መልእክት ምንድን ነው? |
| | ለመገመት | ታሪኩ ቢቀጥል፣ ምን የሚሆን ይመስላችኃል? |
| | ለማጠቃለል | ታሪኩን በራሳችሁ አባባል ልትነግሩኝ ትችላላችሁ? |
| | የታሪኩን ዋና ድርጊቶችን ለማወቅ | በታሪኩ ውስጥ ወሳኝና ዋና ድርጊቶች ምን ምን ይመስሏችኋል? ለምን? |

## አምስት ንባብ

አምስት ንባብ ለተለያዩ ትምህርታዊ አገልገሎት/ዓላማዎች ይውላል፡፡ ይህ ዘዴ ተማሪዎችን በማንበብ እንደዲደሰቱ፣ ከስጋት ነጻ የትምህርት አካባቢ በመፍጠር ጭንቀትን አስወግዶ ውጤታማ ለማደረግ፣ ከውድቀት ፍርሀት ነጻ የሚያደርግ፣ እንደ ልጆቹ የንባብ ችሎታ የተዘጋጀ አሰደናቂ፣ ጠያቂና አስደሳች መሳሪያ ነው (ዋድስሮዝ፣ 2008)፡፡ አምስት ንባብ የቀደመ እውቀትን መሰረት በማድረግ ያነሳሳል፤ አዳምጦ የመረዳት ክሂልን ያዳብራል፤ የንባብ ፍሰትን ጠብቆ ለማንበብ ሞዴል ይሆናል፤ የንግግር ቋንቋ መዋቅርና አዳዲስ ቃላትን ያስተዋውቀል፤ ስዕልንና ቃላትን ያስተሳስራል፡፡

አተገባበሩ፦

- ለአንባቢዎቹ የማዳመጥ ደረጃ ተስማሚ የሆነ መጽሀፍ መምረጥ፤
- የመጽሀፉን ሽፋንና ርዕስ መሰረት በማድረግ፣ መጽሀፉ ስለምን እንደሆነ ተማሪዎቹን እየጠየቁ ማስተዋወቅ፤
- አጋዥ የንባብ መጽሀፉን በትክክል፣በፍጥነትና በተገቢ አገላለጽ ማንበብ፤
- በንባቡ መሃል ቆም እያሉ ምን እንደተነበበና በቀጣይ ምን እንደሚከሰት መጠየቅ፤
- ከምንባቡ በኋላ ተማሪዎቹ ታሪኩን ለጓደኞቻቸው ወይም ለሁሉም የክፍሉ ተማሪዎች እዲናገሩ፣ ገጸባህሪውን እንዲገልጹ፣ እና አዲስ አጨራረስ እዲፈጥሩ ማድረግ፤

## የጥንድ ንባብ

ተማሪዎች ንባብን በቃል አሰምቶ ለሌሎች ማንበብን በተደጋጋሚ ለመለማመድ አጋጣሚውን ካገኙ የተሻለ አንባቢ ይሆናሉ። ለጓደኞቻቸው፣ ለወላጆቻቸው፣ ወይም ለሌላ ሰው ካነበቡ፣ ለሌሎች ለማንበብና ሌሎችን ለማዳመጥ ልምድ ያገኛሉ።

አተገባበሩ፦

- በቅድሚያ ተማሪዎችን በአንስተኛ ቡድን/ትንሽ ቁጥር መመደብ፤
- የአጋዥ የንባብ መጽሀፉን እያንዳንዳቸው ተራ በተራ እንዲያነቡ ያድረጉ፤
- ይህን አካሄድ በቅድሚያ አነስተኛ ቡድን ወይም አነስተኛ ቁጥር የተመደቡ ተማሪዎችን በመጀመሪያ በማለማመድ እንደ ሞዴል ይውሰዱ
- ንባቡ ካስቸገራቸው ተማሪዎቹ እርስ በእርስ እንዲረዳዱ ያደርጉ፤ ድምፅና ፊደል የመለየት ዘዴን ይከልሱ።
- በጥንድ ንባብ ጊዜ የተሻለ የማንበብ ችሎታ ያለው ወይም ከተማሪዎች መካከል ምሳሌ የሚሆን ካለና እንዴት ምሳሌ ሊሆን እንደሚችል ይጠይቁ። ለምሳሌ፦ በተለያየ የድምጽ ቃና ያነበበ፣ ቃላትን በትክክል ያነበበ፣ በእያንዳንዱ አረፍተ ነገር መጨረሻ ተገቢ እረፍት ያደረገ፣
- ሌሎች ጥያቄችን በመጠየቅ ማበረታታት፤ ለምሳሌ ያስደሰተህ/ሽ ክፍል የትኛው ነው? መጨረሻውን እንዴት ልትቀይረው/ልትቀይሪው ትችል /ትችይ ነበር?
- ተማሪዎች በቃል ሲያነቡ ጓደኞቻቸው እንዲያዳምጧቸው በማድረግ ምዘና ማካሄድ

## ህትመት ጽንሰ ሃሳብ

የህትመት ጽንሰ ሃሳብ ማለት ጽሁፉን ከግራ ወደቀኝ፣ ከላይ ወደታች ማንበብ፣ በቃላት መካከል የሚኖር ክፍት ቦታ፣ ስርዓተ ነጥቦችን መገንዘብ፣ የመጽሀፉ ሽፋን፣የርዕስ ገጽ፣ ቃላት፣ አረፍተ ነገሮችና ሌሎች ገጽታዎችን ያጠቃልላል። ለአንድ አንባቢ የህትመት ጽንሰ ሀሳብ ግንዛቤ መኖር አጋዥ የንባብ መጽሀፉን በሚገባ ለመረዳት ያግዛል። የህትመት ጽንሰ ሃሳብ አቀላጥፎ ለማንበብና አንብቦ ለመረዳትም እግዛ ያደርጋል።

አተገባበሩ፦

- ምሳሌ የሚሆን አጋዥ የንባብ መጽሀፍ በመጠቀም የህትመት ጽንሰ ሃሳብ እንዴት እንደሚጠቀሙበት ማሳየት።
- ተማሪዎች የአመልካች ጣታቸውን ወደ አየር እንዲያመለክቱ በማድረግ ይህን ጣታቸውን በመጠቀም አጋዥ መጽሀፉን የተለያዩ ክፍሎች እንዲያመላክቱ መጠየቅ፤
- ተማሪዎቹ የአጋዥ መጽሀፉን ሽፋን፣ የመጀመሪያና የመጨረሻ ገጽና ሌላ ተጨማሪ በመጽሀፉ የሚገኙ መረጃዎችን እንዲያመለክቱ መጠየቅ፤
- የመጽሀፋቸውን ገጽ እንዲገልጡ ማድረግ፤
- ተማሪዎቹን ከመጀመሪያው ገጽ የመጀመሪያውን ቃል እንደያሳዩ ማድረግ፤
- ተማሪዎቹን ስርዓተ ነጥቦችን እንዲያሳዩ ማድረግ፤
- ተማሪዎች የተሻሉ አንባቢዎች እንዲሆኑ እያንዳንዱን ቃል ከማመላከት ይልቅ በአረፍተ ነገር ውስጥ ያሉትን ቃላት በጣታቸው ከአረፍተ ነገሩ የመጨረሻ ከስርዓተ ነጥቡ እኪደርሱ ድረስ እንደያሰምሩ ማደርግ የተሻለ ነው። እንደህ ዓይነቱ ተግባር አቀላጥፎ ማንበብን ለማሻሻል ይረዳል።
- የህትመት ጽንሰ ሃሳብ ግንዛቤ እሰኪማሩ ድረስ እንደህ አይነቱ ተግባር ተጠናክሮ መቀጠል አለበት።

## ድምፃችን፣ ፊደላትንና ተዘውታሪ ቃላትን የመለየት ስልት

ተማሪዎች ድምፀታዊ አጋዥ የንባብ መጻህፍትን በሚጠቀሙበት ጊዜ ለዚህ ተግባር ተብሎ የተለየና ተስማሚ የሆነ የማስተማር ስልት በመተግበር ተዘውታሪ ቃላትን የመማር አቅማቸውን ማሳደግ ይቻላል:: ለዚህ ተግባር የተለዩና ውጤታማ የሆኑ የማስተማር ስልቶችን መጠቀም ህጻናቱ ሥርዓተ- ድምጽን እንዲገነዘቡ፣ ድምፆችን እንዲለዩ እና የንግግር ቋንቋቸውን እንዲያሻሽሉ ያግዛቸዋል:: በመሆኑም ተማሪዎች ስልቶቹን ደጋግመው በመለማመዳቸው የተነሳ በግላቸው በሚያነቡበት ወቅት ስልቶቹን የራሳቸው የንባብ ስልቶች አድርገው እንዲጠቀሙባቸው ለማድረግ እነዚህን የንባብ ማስተማሪያ ስልቶች በተደጋጋሚ ማስተማር ይገባል::

አተገባበሩ፦

- ቃላትን በትንሹ በመከፋፈልና እንደገና በማገናኘት ማንበብ (መነጠልና ማጣመር)፦ ተማሪዎቹ ከቃላት ክፍልፋይ ቃላትን በማውጣት ወይም ቃላትን በመከፋፈል በቀላሉ ማንበብ፤ ሌላውን ክፍል በመጨመር ማንበብ ለምሳሌ፦ "አስመጣ" የሚል ቃል ቢኖር፣ ተማሪዎቹ "መጣ" የሚለውን ማንበብ ቢችሉ "አ" እና "ስ" ነጣጥለው በማንበብ "መጣ"ን በመጨመር "አስመጣ" ብለው በጣም በቀላሉ ማንበብ ይችላሉ::
- አውዳዊ ፍንጭ፦ ተማሪዎች የማያውቋቸው ቃላት ትርጉም በአረፍተ ነገር ውስጥ ሲፈልጉ፣ ትርጉሙን የማያውቁትን ቃል በመዝለል ሌላውን የአረፍተ ነገር ክፍል ያንብቡ፤ አንዳንድ ጊዜ ከሚታወቁት ቃላት የማይታውቁትን ቃላት ፍች ለማወቅ የሚያስችል ፍንጭ ማግኘት ይችላሉ::
- ማስፋፋት፦ ተማሪዎች የቃላቱን ድምጾች መጥራት፤ እሷ/እሱ ድምጾችን መለየት ካልቻሉ እያንዳንዱን ድምጽ በተናጥል በተደጋጋሚ በመጥራት መለማመድና ከዚያም እንደገና በማጣመር ማንበብ... ለምሳሌ "ዘመረ" የሚለውን ቃል ማንበብ ባይችሉ "ዘ-መ-ረ" በማለት ነጣጥሎ ማንበብ፣ በተዳጋጋሚ "ዘዘዘዘዘ.... መመመመመ... ረረረረረ..." እያሉ በመጥራት መለማማድና እንደገና በማጣመር "ዘመረ" ብሎ ማንበብ::
- መለየት፦ ከሥዕሎች ላይ ፍንጮችን በመለየት ቃላትን ማንበብ ይችላሉ::
- እንደገና ማንበብ፦ ተማሪዎች ቃላትን ወይም አረፍተ ነገሮችን ደጋግመው በማንበብ የተሻለ ስሜት የሚሰጥ የንባብ ደረጃ ላይ ይደርሣሉ
- መጀመሪያና መጨረሻ፦ ተማሪዎች ያልተለመዱ ቃላትን ለማንበብ የመካከሉን ድምጽ ከማንበባቸው በፊት የመጀመሪያውንና የመጨረሻውን ድምጽ መጥራት፤

## ስዕል በመጠቀም ማስነበብ

ሰዕልን በመጠቀም ማንበብን ማስተማር አንባቢዎች ከመጽሀፉ ስዕሎች የሚያገኙትን ፍንጭ በመጠቀም ከቀደመ ዕውቀታቸው ጋር በማያያዝ የታሪኩን ጽንሰ ሃሳብ ለመረዳት ያግዛቸዋል:: ይህ ደግሞ አንባቢዎች አጋዥ የንባብ መጽሀፍትን ለማንበብ ያነሳሳቸዋል፤ ይዘቱን ለመረዳት አስቀድሞ/ከማንበበባቸው በፊት ያዘጋጃቸዋል፤ ለማንበብም ያነሳሳቸዋል:: ከማንበባቸው በፊት ስለአጋዥ የንባብ መጽሀፉ ግንዛቤ እንዲኖራቸውም ያደርጋል::

የአተገባበር ቅደም ተከተል

- ተማሪዎቹ የመጽሀፉን ሽፋን በጥልቅ እንዲመለከቱ መጠየቅ፤ከዚያም ታሪኩ ምን ሊሆን እንደሚችል ከጓደኛቸው ጋር እርስ በእርስ እዲነጋገሩ መጋበዝ ወይም የክፍሉን ተማሪ በሙሉ ማወያየት (እንዲገምቱ ማድረግ)፤
- ተማሪዎች ከመጀመሪያው ገጽ ጀምረው እስከመጨረሻው ገጽ ስዕሉን እንዲመለከቱ ማድረግ
- ተማሪዎቹ ስዕሉን እያዩ ወይም አይተው ከጨረሱ በኋላ ያዩትን እንዲገልጹ ማድረግ ገጸ ባህሪያቱ፣ድርጊቱና መቼቱን ማንና ምን ሊሆን እንደሚችል ማወያየት፤
- ሰዕሉን ካዩ በኋላ ግምታቸው ትክክል መሆን አለመሆኑን መጠየቅ

- ስዕሉን ከተመለከቱ በኋላ ታሪኩ ስለምን ሊሆን እንደሚችል በዝርዝር መጠየቅ
- ስዕሉን ከተመለከቱ በኋላ ታሪኩ ስለምን ሊሆን እንደሚችል በዝርዝር እያስታውሱ ስለገጸ ባህሪያቱ፣ መቼቱና ድርጊቱ በአረፍተ ነገር ደረጃ እንዲናገሩ ማድረግ።

## ከጓደኛ ጋር በየተራ መናገር

በየተራ መናገር ሁሉንም የቋንቋ ክሂሎችንና የማሰብ ችሎታን ለማዳበር ይጠቅማል። መደበኛውን የእርስ በርስ ንግግር የሚከተል በመሆኑ ስለ ውይይት የዕለት ተዕለት አካሄድ ግንዛቤ ያስጨብጣል።

የአተገባበር መመሪያ

- ተማሪዎችን ጥያቄ በመጠየቅ ወዲያው እንዲመልሱ ማድረግ፣ ስለዚህ ተማሪዎቹ ከአጋዥ የንባብ መጽሀፉ ጋር በሚገናኝ ሃሳብ እንዲወያዩ ማድረግ፤ ለምሳሌ፦ ተስፋዬና ትዕግስት እንደሚረዳዱ ታስባላችሁ...
- ተማሪዎችን ከጓደኞቻቸው ጋር እንዲጣመሩ ማድረግ
- ተማሪዎቹን በጥያቄዎች እንዲወያዩ ማድረግ ወይም ለጓደኞቻቸው ፈጣን ምላሽ እንዲሰጡ ማድረግ፤ ተማሪዎቹ ተራ በተራ ሀሳብ እንዲለዋወጡ ማበረታታት፣ ሃሳብ ማብራራት፣ ጥያቄውን ግልጽ ማድረግና ጥሩ አድማጭ መሆን፤ እንደገና ለመናገር ይጠቅማል።
- ለተማሪዎች በቂ የውይይት ጊዜ መስጠት
- የተማሩትን እርስ በእርስ እንዲነጋገሩበት ማድረግና የተገኘውን ሃሳብ ለሁሉም የክፍል ተማሪዎች እንደናገሩ መጠየቅ
- ይህን ዘዴ ለሁሉም ክፍል ተማሪዎች ለማስተዋወቅ ትንሽ ደቂቃዎችን ወሰዶ መለማመድና ምሳሌ ሲያስፈልግ መጠቀም ይቻላል።

## የቀደመ እውቀት

ይህ ብልሃት ተግባራዊ የሚሆነው ተማሪዎች ከዚህ በፊት ስለ አጋዥ የንባብ መጽሀፉ ይዘት ያላቸውን እውቀት ለመቀስቀስ ርዕሱና ስዕሉን መሰረት በማድረግና ተጨማሪ ገለጻ በመስጠት ነው። መምህራን ወይም ፈቃደኛ አስነባቢዎች የማያውቁትን ነገር በማሳወቅ አውቀት በመገንባት ሊረዷቸው ይችላሉ። የልጆችን የቀደመ እውቀት ለማሳደግ አጭር ገለጻ በማድረግና ሃሳቦችን ከስዕሎቹና ከርዕሱ ጋር በማያያዝ ልጆችን መርዳት ይቻላል።

የአተገባበሩ ሂደት

- አጋዥ የንባብ መጽሀፉን ለተማሪዎች በማስተዋወቅ ስለ ርዕሱ ምን እንደሚያውቁና በመጽሀፉ ሽፋን ወይም በውስጥ ያለውን ስዕል በማሳየት የሚውቁትን መጠየቅና ዛሬ የምናነበው ይህን ርዕስ ነው ማለት ያስፈልጋል
- ርዕሱንና በጽሀፉ ሽፋን ያለውን ስዕል ተመልክቱ፣ ምን እንደምታውቁ ተናገሩ(ወይም ለጓደኛችሁ ንገሩ)
- በጥንድ የሚሰሩ ከሆነ፣ ከውይይታቸው የተለያየ ሃሳብ እንዲለዋወጡ መጠየቅ
- ከተማሪዎቹ መልስ ስለ ምንባቡ ጽንሰ ሃሳብ ምን እንደማያቁና ምን እንዲሚያውቁ መጠየቅ
- እውቀታቸው ውስን ከሆነ፣ ከአጋዥ የንባብ መጽሀፍ ስዕሉን በማሳየት ሃሳቡን እንዲገልጹ ማድረግ ወይም ሌላ አጋዥ የንባብ መጽሀፍ ዝግጁ ማድረግ፤

## ፈጣን ጽህፈት (በፍጥነት መጻፍ)

ፈጣን ጽህፈት ተማሪዎች የሚያውቁትን በማሰብ ከሚማሩት ሃሳብ ጋር የሚገናኝ አዲስ መረጃ እንዲያገኙ ያግዛል። ፈጣን ጽህፈት አቀላጥፎ መጻፍ፣ቃላትና መረዳትን ያሻሽላል። ይህ ሂደት በተከታታይነት ከተተገበረ ተማሪዎች ስለ ርዕስ ጉዳዩ እንዲማሩ፣ የበለጠ እንዲነሳሱ፣ ጽሁፋቸው በጣም ዝርዝርና የሃሳብ ፍሰቱ የጠበቀ እንዲሆን ያደርጋል።

የአፈጻጸም ሂደት

- ለተማሪዎች የሚጽፉበትን ሃሳብ በቃል በመንገር ስለ አጋዥ የንባብ መጽሀፉ እንዲጽፉ ማድረግ
- ተማሪዎቹ ስለርዕሰ ጉዳዩ የሚያስቡትን ማንኛውንም ነገር ከሶስት እስከ አምስት ደቂቃ በመስጥት እንዲጽፉ መጠየቅ
- ተማሪዎች ስለቋንቋው ወይም ድምጹ ምንም ሳይጨነቁ ከተማሩት ያገኙትን ሃሳብ በወረቀት እንዲጽፉ ማድረግ
- ተማሪዎቹ የጻፉትን ለክፍሉ ተማሪዎች፣ለጓደኞቻቸው ወይም ለየቡድኖች እንደያካፍሉ መጠየቅ
- ተማሪዎች ስለአጋዥ የንባብ መጽሀፍ ርዕስ እንዲያነቡ ወይም እንዲያዳምጡ ካደረግን በኋላ አጋዥ የንባብ መጽሀፉን ለተማሪዎች ማንበብ።
- ከንባብ ወይም ከማዳመጥ በኋላ ተማሪዎች ከአጋዥ የንባብ መጽሀፉ ያገኙትን ሃሳብ መነሻ በማድረግ ስለሚያውቁት ማንኛውም ጽንሰ ሃሳብ እንዲስቡ ማድረግና ከሶስት እስከ አምስት ደቂቃ በመስጠት እንደጽፉ ማድረግ።
- ተማሪዎች አጋዥ የንባብ መጽሀፉን ከማንበባቸውና ከማዳመጣቸው በፊትና ካነበቡና ካዳመጡ በኋላ እንዲጽፉ ማድረግና ማወዳደር
- ተማሪዎቹ ስለርዕሰ ጉዳዩ ከተማሩ በኋላ ምን እንደጻፉ ሃሳባቸውን እንዲያካፍሉ ማድረግ
- ለምሳሌ፦ ተማሪዎች ለሶስት ደቂቃ እንዲጽፉ "ብክለት" የሚለውን ርዕስ መንገር፤ ስለብክለት የሚያውቁትን እንደሚመዘግቡ ይጠበቃል፤ ስለብክለት የሚያወራው አጋዥ የንባብ መጽሀፍ ከተነበበ በኋላ ተማሪዎችን ስለ ብክለት ሚያውቁትን ማንኛውም ነገር ከሶስት ደቂቃ ባላነሰ እንደገና እንዲጽፉ መንገር፤ ከዚያም ተማሪዎች ስለብክለት የጻፉትን ሃሳብ ለጓደኞቻቸው እንደያካፍሉ ማድረግ፤

## ደብዳቤ መጻፍ

ደብዳቤ መጻፍ ተማሪዎች ሀሣባቸውን ለሌሎች በጔደኛነት ስሜት የሚገልጹበት ጥሩ መንገድ ነው። ደብዳቤ አራት የተለያዩ ክፍሎች አሉት። እነዚህም ቀን፣ ሰላምታ፣ ሀተታና መደምደሚያ ናቸው። የጓደኛ ደብዳቤ ረቂቅ ከጻፉ በኋላ ተማሪዎች ደብዳቤያቸውን የጋራ እርማት በማድረግ ለሌሎች ሀሳባቸውን ሊያካፍሉ ይችላሉ። ተማሪዎች በአጋዥ መጽሐፉ ውስጥ ለሚገኝ የታሪክ ገፀ-ባህርይ ወይም ፅንሰ ሀሣብ ደብዳቤ መጻፍም ይችላሉ።

የአተገባበር ሂደት

- ስለደብዳቤ አጻጻፍ ዓላማና የደብዳቤ ክፍሎችን ማስተዋወቅ
- የተሟላ ደብዳቤ በማሳየት በእያንዳንዱ ክፍል መነጋገር
- ተራኪ ወይም መረጃ ሰጭ አጋዥ የንበብ መጽሀፍ ማንበብ
- ከአጋዥ የንባብ መጽሀፉ አንዱን ገጸ ባህሪ ወይም ትንሽ ሃሳብ በመውሰድ ደብዳቤ እንዲጽፉ መጠየቅ
- ተማሪዎቹ የጻፉትን ለተወሰነ ቡድን ወይም ለሁሉም የክፍሉ ተማሪዎች እንዲያነቡ መጠየቅ
- በተማሪዎቹ ስራ ሁሉም የደብዳቤ ክፍሎች የተካተቱ መሆናቸውን ማረጋገጥ
- ከተቻለ የተጻፈውን ፅሁፍ (ደብዳቤ) ለክፍሉ ተማሪዎች ማሣየት

## የቃላት አደራደራቸው የተዘበራረቁ ዓረፍተነገሮች

አጠቃቀም፡- ከንባብ በፊት፣ በንባብ ጊዜ እና በኋላ

የተዘበራረቀ አረፍተነገር ተማሪዎች ስለቃላት ቅደም ተከተልና ስለስርአተ ነጥቦች ለማስተማር ይጠቅማል። ይህ ተግባር በማንበብና መጻፍ ወቅት በጥልቅ ማሰብን፣መገመትን፣የሰዋሰው እውቀት (ስርዓተ ነጥብ፣ የቃላት ቅደም ተከተል)ና ቅደም ተከተላዊ መረዳት ችሎታን ያዳብራል።

የአተገባብር ሂደት

- ከመጀመሪያው፣ከመካከልና ከመጨረሻ ከተጨማሪ የንባብ መጽሀፍ አንድ ጠቃሚ አረፍተነገር መፈለግ፤ ከተመረጠው ዐረፍተ ነገር የተገኘውን ቃል በጥቁር ሰሌዳ ቅደም ተከተል አዛብቶ መጻፍ
- ተማሪዎች ቃላትን በትክክለኛ ቅደም ተከተል አስገብተው ያተስተካከሉትን አረፍተ ነገር በጥቁር ሰሌዳ መጻፍ
- ተማሪዎች ውጤታማ ከሆኑ፣ ተጨማሪ አሻሚ/የተዛቡ አረፍተ ነገሮችን ከአጋዥ የንባብ መጽሀፍ በማውጣት በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ተማሪዎቹ እንዲያስተካክሉት መጠየቅ፤እንደተማሪዎቹ ችሎታ አሻሚ/ቅደምተከተላቸው የተዛባ አረፍተ ነገሮችን በጥቁር ሰሌዳ ወይም በደብተራቸው እንዲጽፉ በማድረግ እንዲያስተካክሉ ማድረግ፤
- የተስተካከሉትን አረፍተ ነገሮች መመልከትና ተማሪዎቹ አጋዥ የንባብ መጽሀፉ ስለምን ሊሆን እንደሚችል እንዲገምቱ ማድረግ፤
- አጋዥ የንባብ መጽሀፉ ከተነበበ በኋላ ግምታቸው ትክክል መሆኑንና አለመሆኑን እንዲገልጹ ማድረግ፤
- ከተነበበ በኋላ ተማሪዎቹ ያላስተካከሉትን አረፍተ ነገሮች በመጠቀም የታሪኩን ክፍል እንደገና በቅደም ተከተል እንዲናገሩ ማድረግ፤አረፍተነገሮቹን በቅደም ተከተል በደብተራቸው እንዲጽፉ ማድረግ ወይም ከጓደኞቻቸው ጋር ሃሳብ እንዲለዋወጡ ማድረግ።
- ይህ ተግባር መገመት/መተንበይ ሚለውን ወደኋላ በማዘግየት አጋዥ የንባብ መጽሀፍ ከተነበበ በኋላ ሊከናወን ይችላል።

## መገመት፣ ምላሽ፣ ማረጋገጥ/ማጠናከር፣ መጻፍ

የመገመት፣ምላሽ የመስጠት፣ የማረጋገጥ/የማጠናከርና የመጻፍ ሂደት በተከታታይነት የመሚከሰተው ተማሪዎች ያነበቡትን ጽሁፍ ስለመረዳታቸው እራሣቸውን እንዲገመግሙ ነው። ሂደቱ የቀደመ እውቀትን ለመቀስቀስና መረዳትን ለማሳደግ ይረዳል።

አተገባበሩ፦

ደረጃ 1፦ አጋዥ የንባብ መጽሀፉን ርዕስ ያንብቡና የሽፋኑን ስዕል ለተማሪዎች ያሳዩአቸው።

ደረጀ 2፦ የርዕሱን ወይም የሽፋኑን ሰዕል ተመልክተው አጋዥ የንባብ መጽሀፉ ስለምን እንደሆነ ተማሪዎቹ እንደገምቱ ያድርጉ።

ደረጃ 3፦ አጋዥ የንባብ መጽሀፉን ድምፅ በማሰማት ያንብቡ።

ደረጃ 4፦ በንባብ ጊዜ ቆም እያሉ ግምታቸውን የሚያረጋግጥ ወይም የሚያፈርስ ነገር ማግኘታቸውን ይጠይቁ።

ደረጃ 5፦ ከንባብ በኋላ ግምታቸው ትክክል መሆኑንና አለመሆኑን በጽሁፍ እንዲገልጹ ያድርጉ። (በግል ወይም በጥንድ)

## እንደገና መንገር

እንደገና መናገር የሚያገለግለው ለተራኪ ጽሁፍ ቢሆንም ለመረጃ ሰጭ ጽሁፍምመጠቀም ይቻላል፡፡ እንደገና መናገር ማለት ተማሪዎች የሰሙትን ታሪክ በራሳቸው አገላለጽና ቃደምተከተሉን ሳያዛቡ ታሪኩን እንደገና መናገር ማለት ነው፡፡

አተገባበሩ፦

- አንድ አጋዥ የንባብ መጽሀፍ ከተነበበ በኋላ ተማሪዎቹ እንዴት እንደተነበበ እንዲያስቡ ማድረግ፤ የታሪኩን መጀመሪያ፣ መካከልና መጨረሻ እንዲያስተዉሉ ወይም ስለገጸባህሪያቱ፣ መቼቱ፣ ድርጊቱ፣ ግጭቱ፣ መፍትሔው እንዲያስቡ ማድረግ፡፡
- ታሪኩን እንደገና መንገር እንዴት እንደሚቻል አጋዥ የንባብ መጽሀፉን በቃል ሲያነቡ መጀመሪያ፣ቀጥሎ፣ቀጥሎ...በመጨረሻ የሚከሰቱን ድረጊቶች ከተማሪዎች ጋር በመሆን በጥቁር ሰሌዳ መመዝገብ፤ የተጻፉት በቅደም ተከተል መሆንና አለመሆኑን ካዳመጡት አንጻር እንዲናገሩ ማድረግ፤ እንደገና መሆን ታሪኩ የተፈጸመበትን ቅደም ተከተል ጠብቆ መነገር እንዳለበት ማስታወስ፡፡
- አንዳንድ ተማሪዎችን ወደፊት እንዲመጡ ማድረግና በመዘገቡበት ቅደም ተከተል እንደገና እንደናገሩ ማድረግ፡፡
- ተማሪዎችን በመምረጥ አጋዥ የንባብ መጽሀፉን ላላዩ ወይም ላላነበቡ ጓደኞቻቸው እንደገና እንዲናገሩ ማድረግ፤ የመረጡትን ታሪክ ቅደም ተከተሉን ሳያዛቡ እንደገና እንዲናገሩ ማዘዝ፡፡
- አስፈላጊ ከሆነ የምንባቡን ክፍል ወዲያውኑ እንዲያስታውሱ ማድረግ፤ አለበለዚያ በመጀመሪያ፣ በመካከልና በመጨረሻ ምን እንደተፈጸመ፣ ችግሩንና መፍትሄውን፤ወይም ቀጥሎ... ምን ተፈጸመ እያሉ ክፍት ጥያቄዎችን ለክፈሉ ተማሪዎች መጠየቅ (ምን የምትነግሩኝ ነገር አለ?፣የምትነግሩኝ ተጨማሪ ነገር አለ? የመሳሰሉትን መጠየቅ)
- ተማሪዎቹ ከአጋዥ የንባብ መጽሀፉ ያነበቡትን እንደገና ለመናገር የተዘጋጁ መሆናቸውን ካረጋገጡ በኋላ ለጓደኞቻቸው እንዲናገሩ ማድረግ፤ ተማሪዎች የሚያነቡት ጽሁፍ ከአቅማቸው በታች ወይም በአቀማቸው/በደረጃቸው ከሆነ ታሪኩን ለማንበብ አይታገሉም/አይቸገሩም፤ ይህም አድማጮች ታሪኩን እንዲረዱትና እንደገና ለመናገር የሚያስችሉ ብዙ ጠቃሚ ሁኔታዎች እንደፈጠሩ ያግዛል፡፡
- ይህን ክሂል ተማሪዎቹ እስኪለምዱት ብሎም ታሪክ እስኪያዋቅሩና በቅደምተከተል እስኪያሰቀምጡ ድረስ መደበኛ ልምምድ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## እንደገና ማንበብ

ከንባብ በኋላ መጠቀም

አጋዥ የንባብ መጽሀፍትን እንደገና ማንበብ አቀላጥፎ ማንበብን፣ የቃላት አውቀትን፣ እና መረዳትን ያሻሽላል፡፡ ተማሪዎች እንደገና ሲያነቡ ቃላትን ለመገንዘብ እየቀለለ፣ እየቀለለ ይመጣላቸዋል፡፡ በእያንዳንዱ ተደጋጋሚ ንባብ የተነሳ ቓላትን ያለ ብዙ ድካም መገንዘብ ስለሚችሉ ህፃናት ጊዜያቸውን አንብቦና አድምጦ መረዳት ላይ እንዲያውሉ ያግዛቸዋል፡፡

አተገባበሩ፦

- አጭር አጋዥ የንባብ ጽሁፍ ከተነበበ በኋላ፣ ተማሪዎች ደግመው ያንቡት፤እንደገና ለሶስተኛ ጊዜ ንቡት፤ ያለምንም ችግር አስከሚያነቡ ድረስ ለሌላ ተማሪ፣ለመምህር፣ ለተወሰነ ቡድን ወይም ለሁሉም የክፍል ተማሪዎች ደጋግመው ያንብቡ፡፡
- ተማሪዎችን በመጀመሪያ እና በሶስተኛ ንባባቸው ያላቸውን ለውጥ ይጠይቋቸው፡፡

- የመጀመሪያው ንባብ ከሶስተኛው ንባብ እንዴት እነደሚለይ ይጠይቋቸው:: የንባብ ፍጥነታቸው ጨመረ? ታሪኩን የበለጠ መረዳት ቻሉ? ሲያነቡ በተሻለ አገላለጽ ነበር?
- ከአጋዥ የንባብ መጽሀፉ የተገናኘ ጥያቄ ሲጠየቁ ተማሪዎቹ መልሱን ካላወቁት አጋዥ የንባብ መጽሀፉን እንደገና እንዲመለከቱ ያበረታቱ፣ ይህ መረዳትን ለማሻሻል የእንደገና ማንበብ ጠቃሚ ገጽታው ነው::

## ቅደም ተከተላዊነት

ይህ ብልሃት ተማሪዎች መረጃዎችንና ድርጊቶችን በቅደም ተከተላቸው በማደራጀት ሀሳብ/ግንዛቤን ለመገንባት/ለማስፋት ነው:: ቅደምተከተል የሚያገለግለው እንደ ምግብ አሰራር ሂደታዊ ያሉ መረጃ ሰጭ ጽሁፎችን ለማብራራት ነው::

አተገባበሩ፦

- አጋዥ የንባብ መጽሀፉን ከማንበባችን በፊትቅደም ተከተላቸው የተዛባ አረፍተ ነገሮችን በጥቁር ሰሌዳ መጻፍ
- አጋዥ የንባብ መጽሀፉን ማንበብ፣ ተማሪዎች ከጎናቸው ለተቀመጠው ወይም በግል እንዲያነቡ መጠየቅ
- ታሪኩን ካነበቡ በኋላ ያነበቡትን እንደገና እንዲናገሩ አንዳንድ ተማሪዎችን መጠየቅ
- በጥቁር ሰሌዳ ላይ ዝርዝሩን በመጻፍ ተማሪዎች ትኩረት እንዲሰጡት ማድረግ
- ተማሪዎች እያንዳንዱን ድርጊት በቅደም ተከተል መሰረት ቁጥር እንዲጽፉበት ማደረግ፤ ወይም በቡድን ሆነው በቁርጥራጭ ወረቀት እንዲጽፉ በማድረግ ማሰራትም ይቻላል:: የቡድኑ ተማሪዎችም ቁርጥራጮችን በማንበብ በአጋዥ መጽሐፍ ውስጥ በተቀመጡበት አግባብ በእጃቸው እየነካኩ በቅደም ተከተል ማስቀመጥ::
- የጻፉትን ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ በቅደም ተከተል እንዲያስቀምጡ ማድረግ::
- አንዳንድ ተማሪዎች ጥቁር ሰሌዳው ላይ ድረጊቶቹን በትክክለኛ ቅደምተከል እንዲጽፉ መጋበዝ::
- የተማሪዎቹስራ ከጥቁር ሰሌዳው ከተጻፈው ጋር ትክክል መሆኑን ማረጋገጥ::

## የድምፅ አወጣጥና ቅላጼ

በተለያየ የድምጽ ቃና ወይም ቅላጼ ድምጽን በማሰማት ማንበብ አቀላጥፎ ለማንበብና አንብቦ ለመረዳት ይረዳል:: ይህ ብልሃት ተማሪዎች እንዲያዳምጡና ተስማሚ አገላለጽ እንዲማሩ ይረዳቸዋል:: ይህ ተግባር በሁሉም የክፍሉ ተማሪ፣በትንሽ ቡድን፣ በጥንድ ሊከናወን ይችላል::

አተገባበሩ፦

- በተለያየ የድምጽ አወጣጥ እና ቃና የሚነበብ ጥሩ አጋዥ የንባብ መጽሀፍ መምረጥና በአንድ ዓይነት የድምጽ ቃና (ድምጽን ሳይቀያይሩ) ና በተገቢው የድምጽ ቃና(ድምጽን እየቀያየሩ) አንብቦ ማሳየት::
- በንባብ ጊዜ ተማሪዎቹን የትኛው በተለያየ የድምጽ ቃና (የድምጽ ከፍታ፣ ዝቅታወዘተ) እንደተነበበ፣ የትኛው ደግሞ እንዳልተነበበ መጠየቅ፤
- በጥቁር ሰሌዳ ሶስት አረፍተ ነገሮችን መጻፍ፤ አንዱ በአራት ነጥብ የሚጨረስ፣ አንዱ በጥያቄ ምልክት የሚጨርስ፣ አንዱ ደግሞ በትዕምሕርተ አንክሮ የሚጨርስ ይሁኑ:: ተማሪዎቹ ስርዓተ ነጥቦቹን እንዲለዩ ማድረግ፤

- ለተማሪዎቹ ስርዓተ ነጥቦቹን ካስተዋወቁ በኋላ እንደየስርዓተ ነጥቦቹ ድምጽዎን እየቀያየሩ ማንበብ፤ እንደየስርዓተ ነጥቦቹ አይነት ተማሪዎቹ የተለያየ የድምጽ ቃና እደሚሰሙ እንዲገነዘቡ መርዳት፤
- ሌላ ተጨማሪ ሶስት አረፍተ ነገሮችን ጥቁር ሰሌዳው ላይ መጻፍ፤አንዳንድ ተማሪዎች እየወጡ ለክፍሉ ተማሪዎች እንዲያነቡ ማድረግ፤ በየአረፍተ ነገሮቹ መጨረሻ ድምጻቸው መቀያሩን መከታተል፤
- ንባቡን የሚያዳምጡት ተማሪዎች በትክክለኛው የድምጽ ቃና ካነበቡ አውራጣታቸውን ወደላይ እንዲያነሱ፣ በትክክላኛው የድምጽቃና ካልተነበበ አውራጣታቸውን ቁልቁል እንደያደርጉ፣ ካላወቁት ደግሞ አውራጣታቸውን መካከል ላይ እንዲያደርጉ ትእዛዝ መስጠት፡፡
- በመጨረሻም ትክክለኛውን የድምጽ ቃና በመጠቀም ለተማሪዎች አጋዥ የንባብ መጽሀፉን ማንበብ፡፡

## ጮክ ብሎ ማሰብ

ጮክ ብሎ ማሰብ ብልሃት ተማሪዎች በሚያነቡበት ጊዜ አትኩሮታቸውንና ሀሳባቸውን እንዲከታተሉ ስለሚያግዛቸው የመረዳት አቅማቸው እንዲሻሻል ያደርጋል፡፡

አተገባበሮች

አጋዥ የንባብ መጽሐፉን ድምፅ በማሰማት ማንበብ

በንባብ ጊዜ በሃሳብ ውስጥ ሆኖ በመናገር እያነበቡ እንዴት ማሰብ እንደሚቻል የማሳየት ሂደት ነው፡፡ ለምሳሌ፡- ስለአንድ ደስተኛ ሰው የሚያነቡ ቢሆን፣ የሚከተለውን ሃሳብ ድምፅዎን እያሰሙ መናገር ይችላሉ፡፡ "ሥዕሉን እንዳየሁት ከሆነ ሰውየው ደስተኛ እንደሆነ መገመት እችላለሁ፡፡ ምክንያቱም ዛሬ ፀሐይዋ በጣም ደማቅ ናት፣ ስለዚህ ሰውየው በእርሻው ውስጥ መሥራት ይችላል፡፡ " በመጨረሻው ገፅ፣ በቀጣዩ ቀን ሰውየው ወደገበያ በመሄድ አትክልት ለመሸጥ ቢዘጋጅም ዝናብ መዝነብ ጀምሯል፡፡ "ምናልባትም ሰውየው ወደገበያ ላይሄድ ይችላል፡፡ ምክንየቱም በዝናቡ ምክንያት ብዙ ሰዎች በገበያ ላይኖሩ ይችላሉ፡፡ " በማንኛውም የታሪኩ ነጥብ ላይ መናገር ይችላሉ፡፡ "ቀጥሎ ምን እንደሚደረግ እገምታለሁ፤ ይገርመኛል" "ለምን ወይም እንዴት--- እንደሆነ ይገርመኛል" "እኔ እንደማስበው ------" በማለት በንባብ ሂደት ሃሳብን እየገለፁ ማንበብ የሀሳብ ፍሰትን እየጠበቁና እየተረዱ ለማንበብ ትልቅ ሚና ይጫወታል፡፡

መምህሩ ጮክ ብሎ እያሰበ ካነበበ በኋላ ተማሪዎች ምን ያህል እንደተከተሉ ምልከታ በማድረግ ከንባብ በኋላ ሃሳባቸውን እንዲያጋሩ ጥያቄወችን ይጠይቋቸው፡፡ ለጓደኞቻቸው የተወሰኑ አረፍተነገሮችን ካነበቡ በኋላ ስለታሪኩ እያሰቡ ጥያቄ ራሳቸውን እንዲጠይቁ በማድረግ አንብበው መረዳታቸውን መቆጣጠር መለማመድ ይኖርባቸዋል ይህ ሂደት ተደጋግሞ መከናወን ይኖርበታል፡፡

በድህረ ንባብ ጊዜ ተማሪዎች አጋዥ የንባብ መፅሃፍን አንብቦ ለመረዳት የሃሳብ ፍሰትን መከታተል ወይም ጮክ ብሎ እየተናገሩ ማሰብ ምን ያህል የተሻለ አንዳገዛቸው እንዲገልፁ መጠየቅ፡፡

ተማሪዎች ሀሳባቸውን ለክፍሉ ተማሪዎች እንዲያጋሩ መጠየቅ

ብልሃቱ ለተማሪዎች ግልጽና ምቹ እስከሚሆንላቸው ድረስ በናሙናነት እያነበቡ ያስረዷቸው፡፡

## ድጋሚ ማንበብ

ድጋሚ ንባብ ማለት የአነባበብ ትዕዛዝን በመከተል የቃል ወይም አሰምቶ ንባብን ደጋግሞ መለማመድና የአነባበብ ግድፈትን በቃል በማረም አቀላጥፎ የማንበብና አንብቦ የመረዳት ክህሎትን የማሻሻል ሂደት ነው፡፡

አተገባበሮች

- ከ50 - 200 ቃላትን የያዘ ደረጃ መጣኝ አጋዥ የንባብ መጽሃፍ ይምረጡ፡፡
- የተመረጠውን ምንባብ ተማሪዎች በፍጥነትና በትክክል እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡

- ተማሪዎቹ በሚያነቡበት ጊዜ የፊደላት /የቃላት ግድፈት፣ በሌላ ቃል የመተካትና፣ የስርዓተ ነጥቡን ጠቀሜታ በትክክል ያለመግለጽ ሂደት መኖር አለመኖሩን ይከታተሉ።
- ተማሪዎቹ ሲያነቡ ስህተታቸውን እንዲያርሙ ከመጀመሪያ ጀምሮ ዓረፍተነገሩን እንደገና በድጋሚ በትክክል እንዲያነቡ በማድረግ ያግዛቸዋል።
- ተማሪዎቹ ምንባቡን በትክክል እስከሚያነቡ ድረስ ደግመው ደጋግመው እንዲያነቡ ያድርጉ በትክክለኛው ፍጥነት እንዲየነቡም ማበረታታት ያስፈልጋል። ምንባቡን አንዴ ወይም ከዚያ በላይ ካነበቡ በኋላ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን በመጠየቅ ሀሳቡን ምን ያህል እንደተረዱ መገምገም ያስፈልጋል።

## ንድፍ መንደፍ

ይህ ብልሃት ተማሪዎች ያነበቡትን ጉዳይ በተጨባጭ መልኩ ንድፍ በመንደፍ /በመሳል፣ አንብበው መረዳታቸውን የሚያረጋግጡበት ነው። የራሳቸውን ወይም የጓደኞቻቸውን የንድፍ ትርጓሜ በቃላቸው ማብራራት ነው። ዋናና ዝርዝር ሀሳቦችን በቅደም ተከተል ለመግለፅ የቀደመ እውቀታቸውን በመቀስቀስና ቃላትን በመጠቀም ምን ያህል እንደተረዱ በንድፋቸው መሰረት ያነበቡትን ወይም ያዳመጡትን አጋዥ የንባብ መጽሀፍ ያቀርባሉ።

አተገባበር

ተማሪዎች አጋዥ የንባብ መፅሀፉን ካነበቡ በኋላ "የገበያ፣ የሱቅ ሁነት በኢትዮጵያ" የሚል ይዘት ያለው ፅሁፍ ቢያነቡ ስለገበያው ሁኔታ በዝርዝር ለማሳየት ንድፍ ይነድፋሉ። የዋጋ ዝርዝሮችን ያካትታሉ፤ ሻጮችን/ ባለሱቆችን፣ የሚገዙ ነገሮችን፣ የግዥ ዝርዝሮችንና ሌሎችንም ጉዳዮች በንድፋቸው ውስጥ ያካትታሉ።

ተማሪዎች ስለፅሁፍ መግለጫ እንዲፅፉ መጠየቅ /በቃል፣ በሀረግ፣ ወይም በዓረፍተ ነገር ደረጃ ሊሆን ይችላል። / ንድፉን ለራሳቸው ወይም ለክፍል ጓደኞቻቸው ማቅረብ ይችላሉ።

የሰሯቸውን ንድፎች ለጓደኛቸው በማቅረብና በመወያየት ሀሳባቸውን እንዲያካፍሉ ማድረግ።

ተማሪዎች የነደፉት ንድፍ ምን የህል ትክክል እንደሆነ ለማረጋገጥ አጋዥ የንባብ መጽሀፉን እንደገና እንዲመለከቱ በማድረግ የሁነቶችን ተከታታይነት በደንብ እንዲነደፉ በመመልከት የመረዳትና በከፍተኛ ደረጃ የማሰብ ብቃታቸውን ማሻሻል መቻላቸውን እንዲያረጋግጡ ማበረታታት ተገቢ ነው።

## መዘርዘር፣ ማባደን፣ ደረጃ መስጠት

ቃላትን ትርጉም ባለው ዓውድለማስተማር በዝርዝር ማስቀመጥ፣ በቡድንና፣ ደረጃ በመስጠት ሶስት ዓይነት ብልሃቶችን መጠቀም ይቻላል። ከዚህ አንፃር ተማሪዎች ቃላትን በየክፍላቸው በመመደብ መማር ይችላሉ።

አተገባበሮች

ደረጃ 1፡ በአጋዥ የንባብ መጽሃፍ ውስጥ አዳዲስ ቃላትን እየመረጡ በጥቁር ሰሌዳ ላይ መጻፍ። /ለምሳሌ ደግሱ/

ደረጃ 2፡ ከቁልፍ ቃሉ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ሌሎች ቃሎችን ከምንባቡ እየመረጡ እንዲናገሩ ተማሪዎች ማበረታታት። /ለምሳሌ፡ ምግብ፣ መመገብ፣ ዝግጅት/

ደረጃ 3፡- በመቀጠል ተማሪዎቹ ቃላቱን በየክፍላቸው እንዲመድቡ ወይም እነዲያባድኑ ማድረግና የደረጃ ስያሜ እንዲሰጧቸው ማበረታታት። /ለምሳሌ፡- ደገሱና ተመገቡ ግሶች ናቸው፤ ምግብና ዝግጅት ደግሞ ስሞች ናቸው/

**የቃላት ጨዋታ**

የቃላት ጨዋታን በመጫወት ቃላትን ማስተማር ይቻላል።

አተገባበሮች

- ከአጋዥ የንባብ መጽሃፉ ቃላትን መምረጥ፣ ተማሪዎች በየትናንሽ ቡድናቸው አንድ አንድ ቃላትን እንዲመርጡ ማድረግ፣
- በቁርጥራጭ ወረቀት ላይ ለእያንዳንዱ የተመረጠ ቃል ተዛማጅ ፍንጭ መጻፍ
- ለክፍሉ ተማሪዎች ከመቅረቡ በፊት በየመቀመጫቸው ተማሪዎች ወረቀቱን እንዲያዩት ማድረግ።
- እያንዳንዳቸው ተማሪዎች ፍንጭ ሰጪ /ጠቋሚ ቃል የተፃፈበትን ወረቀት እንዲያነቡ ማድረግ
- በጠቃሚ ቃሉ ዙሪያ ተማሪዎች በየቡድናቸው እንዲወያዩ ማድረግ።
- በጠቋሚ ቃሉ መነሻነት ተማሪዎች ቃሉን በመገመት እንዲያብራሩ ማድረግ
- በመጨረሻም ጠቋሚ ቃሉ የተመረጠውን ቃል ትርጉም ለመግለጽ ምን ያህል እንደጠቀማቸው ሃሳባቸውን እንዲያካፍሉ ማድረግ።

## 4.6 አጋዥ የንባብ መጻህፍቱን ስንጠቀም ሥርዓተ ፆታንና አካቶነትን ከግምት ውስጥ ማስገባት

### I. አጋዥ የንባብ መፃህፍት

አጋዥ የንባብ መጻህፍትና የመማሪያ መፃህፍት ሲዘጋጁ የሥርዓተ ፆታንና የአካል ጉዳተኞችን አወንታዊ ገፅታ በግልፅ የሚያሳዩ መሆን ይኖርባቸዋል።

ሁሉም አጋዥ የንባብ መፃህፍት የሴቶችንና የወንዶችን፣ የሴት ልጆችንና የወንድ ልጆችን እኩልነት የሚያንፀባርቁ መሆን አለባቸው።

እንደ አስፈላጊነቱም ለአካል ጉዳተኛ ህፃናት ታስበው የተዘጋጁ የአጋዥ የንባብ መፃሕፍት መኖር ይገባቸዋል። (ምሳሌ፡- በብሬይል የተዘጋጁ የንባብ መጽሐፍት)

### II. የቋንቋ አጠቃቀም

የቋንቋ አጠቃቀማችን የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን ያረጋገጠ፣የአካል ጉዳተኞችን በሚገባ ያካተተና እኩል ተጠቃሚ የመሆን መብታቸውን ያከበረ መሆን ይኖርበታል። በተመሳሳይ ሁኔታ የንባብ ጥጎች፣ የንባብና የጽሁፍ ክበባት፣የመጽሐፍ ባንኮችና የንባብ ካምፖች በሙሉ ይህን መሰረታዊ መርህ የተከተሉ መሆን ይገባቸዋል። ስለዚህ መምህራን፣ አመቻቾችና በጎ ፈቃደኞች በሙሉ አበረታች፣አካታችና እኩል ተጠቃሚነትን የሚያንጸበርቅ ቋንቋ በመጠቀም የሁሉንም ተማሪዎች ንቁ ተሳትፎ እና ውጤታማነት ማሻሻል ይጠበቅባቸዋል።

### ተማሪዎችን ማገዝ

አንዳንድ ሴቶች እና አካል ጉዳተኛ ህፃናት እፍረት፣ ምቾት ማጣት ፣ ከተማሪዎቸ ፊት የመቆም ፍርሃት ሊሰማቸው ስለሚችል የእነዚህ ተማሪዎችን የተለየ ፍላጎት መሰረት ያደረገ እገዛ ለመስጠትና ንቁ ተሳታፊ ለማድረግ የሚፈልጉትን ነገር ማሟላት እና ዘገባ ማዘጋጀት አለባቸው።

# 5. በትምህርት ቤት ደረጃ ለሚከናወኑ ተግባራት ወላጆችና የማህበረሰቡ አባላት የሚያደርጉት ድጋፍ

## 5.1 ወላጆችና የማህበረሰቡ አባላት ምን አይነት ድጋፍ ያደርጋሉ? ለምንስ ይጠቅማል?

በትምህርት ቤት ደረጃ በአፍ መፍቻ ቋንቋ መምህሮችና የትምህርት ቤት የበጐ ፈቃደኛ አስነባቢዎች በትብብር ለሚያደርጉት የተማሪዎች የማንበብና የመፃፍ ትምህርትን ወላጆች እና የማህበረሰቡ አባላት ማገዝና መደገፍ ይገባቸዋል፡፡ ወላጆችና የማህበረሰቡ አባላት ልጆች በትምህርት ቤት ደረጃ እነዲያነቡና እንዲፅፉ ለማድረግ ከፍተኛ ሚና ሊጫወቱ ይገባል፡፡

### 5.1.1 የወላጆች ተሳትፎ

ወላጆችና ሞግዚቶች በትምህርት ቤት የሚከናወኑ የንባብ ተግባራትን ማገዝ ይችላሉ፡፡ በንባብ ጥግ ካሉት አጋዥ የንባብ መፅሃፍት በመምረጥና በመዋስ ለልጆች በማንበብ ወይም ልጆቹ ሲያነቡ በማዳመጥ የልጆችን የማንበብና የማዳመጥ ችሎታቸውን ማዳበር ይችላሉ፡፡ ወላጆችና ሞግዚቶች በየቀኑ ልጆቻቸውን በመከታተል የማንበብ ተግባራት እንዲያከናውኑ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ የተለያዩ መረጃዎችን ከመምህሮች ወይም ከአስነባቢዎች በመጠየቅና በመዋስ በትምህርት ቤት ደረጃ የማንበብና የመፃፍ ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ ያግዛሉ፡፡

- ሌላው የወላጆች ተሳትፎ ደግሞ ከትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህሮች፣ መምህር፣ ከመምህራንና በጐ ፈቃደኛ አስነባቢዎች ጋር በመነጋገር በመቀብኘትና በመተባበር የንባብ ተግባራትን መደገፍና ማገዝ ነው፡፡
- ወላጆች ለንባብ ጥግና ለንባብ ክበባት የሚያስፈልጉ የንባብ መሳሪያዎችን እና ማበረታቻዎችን በማቅረብ በኩል ትልቅ ሚና መጫወት ይችላሉ፡፡
- ሴት ልጆችና አካል ጉዳተኞች ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ማድረግ የወላጆች ሀላፊነት ጭምር ነው፡፡ ስለዚህ ወጣት በጐፈቃደኞች፣ የወተመህ አባላትና ሌሎች ከወላጆች ጋር ጥብቅ ትስስር ያላቸው አካላት ሴት ልጆችና አካል ጉዳተኞች በሚገባ እንዲያነቡ ማገዝ ይጠበቅባቸዋል፡፡

### 5.1.2 የማህበረሰቡ ተሣትፎ

የማህበረሰቡ አባላት በትምህርት ቤት ለሚከናወኑ የማንበብ ተግባራት የራሳቸው ጉልህ ድርሻ አላቸው፡፡ ይህም በሚከተለው መልኩ ይገለጻል

- ማህበረሰቡ የአካባቢው ትልቁ መዋቅር እንደመሆኑ መጠን በትምህርት ቤት ውስጥ ያለው የንባብ ጥግ በጥሩ ሁኔታ መያዙን መከታተል ይገባቸዋል፡፡ ለንባብ ጥጉ የሚያገለግሉ የንባብ መፃህፍትንና ሌሎች መሳሪያዎችን የማቅረብ ሃላፊነትም ይኖርባቸዋል፡፡ የንባብና የጽጉፍ መርኃ ግብሮችን ለመደገፍ የሚረዳ እገዛ በጥሬ ገንዘብ ወይም በአይነት አዋጥተው በመለገስ ተሳትፎ ያደርጋሉ፡፡
- ማህበረሰቡ ለበጎ ፈቃደኞች ማበረታቻዎችን በማዘጋጀትና በመስጠት መደገፍ ይችላሉ
- የትምህርት ቤቱ በጐፈቃደኞች የተለያዩ ማህበራዊ በዓላትን በማክበርና በማስተማር ድጋፍ ማግኘት ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ የማህበረሰብ ውይይት፣ የወላጆች ቀን ፣ የሴቶች ቀን፣ የአካል ጉዳተኞች ቀን እና የመሳሰሉትን በማከናወን ስለ ሴት ልጆችና ስለ አካቶ ትምህርት ጠቀሜታ ቅስቀሳና የግንዛቤ ማስጨበጫ ማካሄድ ይችላሉ፡፡
- የትምህርት ቤት በጐ ፈቃደኞች፣ ወመተህ፣ መምህራን፣ ወዘተ በመተባበርና የማህበረሰብ ንቅናቄ በመፍጠር የአካል ጉዳተኛ ህፃናት ያሏቸውን ቤተሰቦች እንዲረዱ ያደርጋሉ፡፡

# አባሪ 1
# (የአሜሪካ ተራደዎ ድርጅት/-------፣ 2012)

## መጽሀፍ ማዘጋጀት

ታማሪዎችን መምህራን በክፍል ውስጥ ሰርተው የሚጠቀሙባቸው የተለያዩ መጽሀፍት ዓይነት አሉ:: እነዚህ መጽሀፍት በክፍል ውስጥ የክፍሉ ተማሪ በጋራ፣ በጥንድ፣ ወይም በግል ጽህፈት ጊዜ ይዘጋጃሉ:: መጽፈፎቹ በግል መጻፋቸው በኋላ ለማንበብ ጠቃሚ ናቸው:: ቀጥሎ አንድ የመጽሀፍ ዓይነት(ሚኒ መጽሀፍ) እንዴት እንደሚዘጋጅ እንመለከታለን:: ሌሎቹ በተጨማሪ ክፍል ይመልከቱ::

የሚኒ መጽሀፍ አዘገጃጀት በቅደም ተከተል፡-

1. ወረቀቱን እኩል ለሁለት ማጠፍና በታጠፈበት መስመር ማጠፍ



2. ከሁለት የተከፈሉትን እንደገና ሁለት ቦታ ማጠፍና በታጠፈበት መቅደድ፤ አሁን አራት ቁርጥራጮች አሉን::



3. አራቱን ቁርጥራጭ አንድ ላይ በማድረግ፣ ማያያዝ፡-



4. ትልቁ ነገር በስቴፐለር ማያያዝ ወይም መስፋት ነው:: እንዲህ ማድረግ ካልተቻለ ወረቀቶችን እኩል አራት ቦታ ምልክት ማድረግ፤
5. አንድ ሴንቲ ሜትር የሚያህል በቀጭኑ መቅደድ፤ ይህ አምስት ቦታ ይሆናል::
6. የመጀመሪያውን በፊት ለፊት ማጠፍ፣ ሁለተኛውን በመጨረሻ ማጠፍ፣ ሶስተኛውን በፊት ለፊት ማጠፍ፣ አራተኛውን በጀርባ ማጥፍ፣ አምስተኛውን በፊት ለፊት ማጠፍ::



7. ከተቻለ ማጣበቅና ማሸግ፣

   በክፍላቸው በሳምንት ውስጥ አምስቱን መጽሀፎች ቢያነቡ፣ በመጽሀፍ ማንበቢያ ጥግ ከ200 ና 300 መጽሀፎች ሊያስፈልጉ ይችላሉ:: እነዚህ ብዙ መጽሀፍት ናቸው:: ነገር ግን ሁሉም ተማሪዎች ጸሀፊ ናቸው፤ አንደኛ ክፍልም ቢሆኑ፣ መርሳት የሌለብን ነገር በዝቅተኛ የክፍል ደረጃ የሚገኙ ልጆች የለመዷቸውን ቴክስቶች ደጋግመው ማንበብ ያስደስታቸዋል::

## ሌላ አይነት መጽሀፍ እንዴት እንደሚሰራ እንመልከት

**ምሳሌ 1፦ ደረጃ በደረጃ መጽሀፍ አዘገጃጀት**

- ሶስት ወይም ከሶስት በላይ ቁርጥራጭ ወረቀቶች
- ክር ወይም ሲባጎ

1. በመጀመሪያ ሶስት ቁርጥራጭ ወረቀቶችን ይያዙ፣ እያንዳንዱ ወረቀት ከሌላው በ3/4 ሴንቲ ሜትር ማነስ ይኖርበታል። መጀመሪያዎቹን ሶስት ደረጃዎች እንመልት፦



2. የመጀመሪያውን ወረቀት በማጠፍ ሌላ ደረጃ አውጡ ፣ ከዚያም ሁለቱን በተመሳሳይ መንገድ ማጠፍ፣ ስድስት ደረጃዎችን ተገኛላችሁ፤



3. በፓንቸር በመብሳት ጫፍ ላይ ሁለት ቀዳዳዎች መስራት፤




4. በቀዳዳዎቹ ቀጭን ክር ማስገባት፤ ሁለቱንም ክሮች አጥበቆ መቋጠር፤

From Making Books with Children by Susan Kapuscinski Gaylord *(www.makingbooks.com)*

# አባሪ 2

## የተግባር እቅድ

ትምህርት ቤት ________________________ ከተማ ________________________ ቀን ___________

ወረዳ ________ ቀበሌ ________

| ተግባር | ሃላፊነት ሚወሰድ ሰው | አስፈላጊ መመሳሪያዎች | መጀመሪያና መጨረሻ ቀን | ስራው እንዴት እንደሚፈጸም |
|---|---|---|---|---|
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |

# አባሪ 3

## ከማንበቢያ ጥግ የመጽሀፍ ማዋሻ ቅጽ

ክፍል ____________

| ተ.ቁ | ቀን | የተማሪው/ዋ ስም | የመጽሀፉ ስም | የመመለሻ ቀን | ፊርማ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | | | | | |
| 2 | | | | | |
| 3 | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |

# አባሪ 4

## ስመጽሀፎች የሚደረግ ጥንቃቄ

1. መጽሀፋችሁን ማስቀመጫ ውስጥ በማድረግ በጥንቃቄ ያዙ፤
2. መጽሀፋችሁን እንስሳት ከማይደርሱበት ቦታ አስቀምጡ፤
3. እባካችሁ ከመጽሀፋችሁ አጠገብ ሆናችሁ አትመገቡ፤አትጠጡ፤
4. መጽሀፋችሁን  በቆሻሻ እጃችሁ አትንኩ፤
5. መጽሀፋችሁን  ከእርጥበት ወይም ከጸሀይ ጠብቁ፤
6. የማታነቧቸውን መጽሀፍት በመጽሀፍ ማስቀመጫችሁ በመጨረሻ አስቀምጡ፤
7. መጽሀፉን በመጽሀፉ የውጭ ገጽ ግለጡ፤ (በመሃል ወይም በመጽሀፉ ውስጥ አትግለጡ)፤
8. **በመጽሩ ላይ አትጻፉ፤**

# አባሪ 5

## ተረቶችን ለልጆች እንዴት መናገር ይቻላል?

ልጆች በተለያዩ ተግባራት ይደሰታሉ። የተለያዩ ድርጊቶችን፣ ቀለማትንና ድምፆችን ይወዳሉ። ልጆች የንባብ ልምዳቸውን እንዲያዳብሩና የማሰብ ብቃታቸውን እንዲያጎለብቱ ወላጆችና አስነባቢዎች ተረቶችን ያንቡላቸዋል። ልጆች ተረት ሲያነቡላቸው ወይም ሲነግሯቸው እንዲደሰቱ የሚከተሉትን ተግባራት በቅደም ተከተል ማከናወን ይጠበቃል።

### 1. ተረቱን ከመናገር/ከማንበብ በፊት

አንዳንድ ጊዜ የልጆች ትኩረት ለአጭር ጊዜ ነው። ስለዚህ ተረቱን ለልጆች ከመናገር በፊት በሚከተሉት ነጥቦች ላይ ትኩረት ማድረግ አስፈላጊ ይሆናል።

#### 1.1 ለልጆች እድሜ የሚመጥኑ ተረቶች መምረጥ

ህፃናት ቀላልና አጫጭር ተረቶችን ይፈልጋሉ። በአብዛኛው በዕድሜያቸው ከፍ ያሉ ልጆች ደግሞ ረዥም ተረቶችን ያዳምጣሉ። ልጆች የተለያዩ ተረቶችን ላያዳምጡ ይችላሉ። የልጆችን የማዳመጥ ብቃት መጠን ለማረጋገጥ የተለያዩ የርዝመት መጠን ያላቸውን ተረቶች በመንገር መፈተሽ ይቻላል።

#### 1.2 የተለያዩ የተረት ክፍሎችን ድምፀት መለየት

1.2.1. ልጆች በተለምዶ ለረዥም ጊዜ ፀጥ ብለው መቀመጥ አይችሉም።

1.2.2. ተረቶችን ሁልጊዜ ለልጆች ለመንገር ጸጥ ያለና የሚመች ቦታ መምረጥ ያስፈልጋል።

1.2.3. ከተቻለ ቋሚ የማንበቢያ ጊዜን መጠቀም። ለምሳሌ ልጆች ሁልጊዜ ከመተኛታቸው በፊት ተረት የሚነበብላቸው ከሆነ ለማዳመጥ ራሳቸውን ያዘጋጃሉ።

1.2.4. ተረትን ለልጆች ከመንገር በፊት ተረት እንደሚነበብላቸው መግለጽ። ልጆች ተረት ሲያዳምጡ እርስ በርሳቸው ሊያወሩ/ሊንቀሳቀሱ ይችላሉ። ይህ ድርጊት የተለመደ ነው።

ስለዚህ የልጆችን ትኩረት ለመሳብ መጣር ያስፈልጋል። ጥያቄዎችን በመጠየቅ ተረቱን ለማዳመጥ ፍላጎት እንዲያድርባቸው ማድረግ ይቻላል።

1.2.5. ከአንድ በላይ ለሆኑ ልጆች ተረቶችን ለመንገር ከተፈለገ ሁሉም ልጆች የሚያዩዋችሁና የሚያዳምጧችሁ መሆኑን ማረጋገጥ አለባችሁ። ለምሳሌ ተረት ተናጋሪው/ዋ በወንበር ላይ በመቀመጥ ልጆች ደግሞ በመሬት ላይ ግማሽ ክብ ሰርተው ፊታቸውን ወደተናጋሪው በማዞር ማዳመጥ ይችላሉ።

### 2. ተረቱ በሚነገርበት ጊዜ

#### 2.1 ልጆች ተረቱን በሚያዳምጡበት ጊዜ የዓይን ግንኙነት መፍጠር አስፈላጊ ነው

2.1.1 አስደማሚ/አስገራሚ ታሪክ ላይ ስትደርሱ ቆም ብላችሁ ልጆቹ ምን ያህል እንደተደመሙ/ እንደተገረሙ መቃኘት ያስፈልጋል።

2.1.2 የሚያስቅ ወይም የሚያስደስት ቦታ ላይ ስትደርሱ ቆም ብላችሁ ልጆችን መመልከት ተገቢ ነው።

2.1.3 የሚያስፈራሩ ድርጊቶች ላይ ስትደርሱ ቆም ብላችሁ ልጆችን እያያችሁ "በፍፁም!"በማለት መናገር።

2.1.4 ጥሩ ድርጊት ላይ ሲደርሱ ወይም ችግሩ የተፈታበት የታሪክ ክፍል ላይ ስትደርሱ ሳቅ በማለት ልጆችን ይመልከቱ።

#### 2.2. እንደየገጸባህሪያቱ አገላለጽ ድምፅን መለዋወጥ

አይጥ የምታወራ ቢሆን "ሲጢጥ" የሚል ድምፅ በማሰማት መግለጽ፣ አንበሳ የሚያወራ ከሆነ ደግሞ የሚያስገመግምና ረጋ ያለ ድምፅ መጠቀምና መግለፅ ተገቢ ነው።

# አባሪ 6

## አጋዥ የንባብ መጻሕፍትን በመጠቀም የክህሎቶች ማስተማሪያ ናሙና ስልቶች አጭር ማጠቃለያ

| ክሂሎች | ስልት | የመፃህፍት ዓይነቶች | የክፍል ደረጃ | የተሰጠው ደቂቃ | ድግግሞሽ |
|---|---|---|---|---|---|
| የፊደላት ድምፆች የቃላት እውቀት አንብቦ መረዳትና | አሰምቶ ንባብ | የአሰምቶ ንባብ መፃህፍት | 1፣ 2፣ 3፣ 4 | 15-30 | በየቀኑ |
| የፊደላት (የድምፆች)፣ የቃላት እውቀት፣ የፍጥነት ንብብና አንብቦ መረዳት | የጥንድ ንባብ | ደረጃ መጣኝና የቃላዊ ንባብ መፃህፍት | 1፣ 2፣ 3፣ 4 | 5-15 | እንደየአስፈላጊነቱ |
| የህትመት (የፅሁፍ) ፅንስ ሃሳብ | የቆምታ ትዕምርቶች ፅንሃ ሃሳብ | ተነባቢና ደረጃ መጣኝ መፃህፍት አንባቢዎች | 1 | 5-10 | በየቀኑ ሆኖ እስከሚጠኑ ድረስ |
| አንብቦ መረዳት የፍጥነት ንባብ | ከሥዕል የምንባብን ሃሳብ መረዳት | ደረጃ መጣኝ፣ አንባቢዎች የሚያነቡትና የቃላዊ ንባብ መፃህፍት | 1፣ 2፣ 3፣ 4 | 5 | እንደየአስፈላጊነቱ |
| የትዕምርተ ድምፆች፣ የድምፆች/ ግንዛቤ ፊደላት፣ የቃላት እውቀት፣ የፍጥነት ንባብ | የተነባቢ/ተተኳሪ ፊደላትን የመለየት ብልሃት | ተነባቢ/ተተኳሪና ደረጃ መጣኝ መፃህፍት | 1፣ 2 | 10 | በየቀኑ |
| የቃላት ዕውቀት፣ አንብቦ መረዳት የፍጥነት ንባብ | ድጋሜ ንባብ | ደረጃ መጣኝ መፅሃፍት | 1፣ 2፣ 3፣ 4 | 3-10 | እንደየአስፈላጊነቱ |
| የፍጥነት ንባብ የቃላት እውቀት አንብቦ መረዳት | የሃሳብ ፍሰት/ ተከታታይነት/ | ደረጃ መጣኝና የቃላዊ ንባብ መፃህፍት | 1፣ 2፣ 3፣ 4 | 5-15 | እንደየአስፈላጊነቱ |
| የፍጥነት ንባብ | ድምፀት/ገለፃ | የደረጃ መጣኝ አንባቢዎች የሚያነቡት የቃላዊ ንባብ መፃህፍት | 1፣ 2፣ 3፣ 4 | 3-5 | በየቀኑ |

| ክሂሎች | ስልት | የመፃህፍት ዓይነቶች | የክፍል ደረጃ | የተሰጠው ደቂቃ | ድግግሞሽ |
|---|---|---|---|---|---|
| አንብቦ መረዳት፣ የቃላት እውቀት፣ የፍጥነት ንባብ | በጥልቀት እያሰቡ ማንበብ | የተነባቢና የደረጃ መጣኝ አንባቢዎች የሚያነቧቸውና የቃላዊ ንባብ መፃህፍት | 1፣ 2፣ 3፣ 4 | 10-15 | እንደየአስፈላጊነቱ |
| የፍጥነት ንባብ | ደጋግሞ ማንበብ | ተነባቢ መፅሀፍት | 1፣ 2፣ 3፣ 4 | 10-15 | እንደየአስፈላጊነቱ |
| አንብቦ መረዳት የቃላት እውቀት | | በአንባቢዎች የሚነበብ ደረጃ መጣኝ | 4 | 10-15 | እንደየአስፈላጊነቱ |
| አንብቦ መረዳት፣ መፃፍ የቃላት እውቀት | ሥዕላዊ መግለጫን መንደፍ | ደረጃ መጣኝ በአንባቢዎች የሚነበብ የቃላዊ ንባብ መፃህፍት | 1፣ 2፣ 3፣ 4 | 5-10 | እንደየአስፈላጊነቱ |
| አንብቦ መረዳት መፃፍ የቃላት እውቀት | መገመት፣ ምላሽ መስጠት፣ ማዳመጥና መፃፍ | ደረጃ መጣኝ በአንባቢዎች የሚነበብ የቃላዊ ንባብ መፃህፍት | 3፣ 4 | 10-15 | እንደየአስፈላጊነቱ |
| የቃላት እውቀት፣ አንብቦ መረዳት፣ መፃፍ | ሠንጠረዦችን ማደራጀት | ደረጃ መጣኝ አንባቢዎች | 3፣ 4 | 10-20 | እንደየአስፈላጊነቱ |
| የቃላት እውቀት | የቃላት ጨዋታ | ደረጃ መጣኝ በአንባቢዎች የሚነበብ የቃላዊ ንባብ መፃህፍት | 2፣ 3፣ 4 | 10 | እንደየአስፈላጊነቱ |